
# ድብልቅልቅ



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከጳውሎስ ኞኞ

# ድብልቅልቅ

ከጳውሎስ ኞኞ

# ማውጫ

ሊቁ። ........................................ 6
እምብዮ።........................................ 15
ሰውዬው።........................................ 23
ሙቶ ሽህ ብር? ........................................ 31
ለ፳፬ ሰዓት........................................ 40
ስለደራሲው በጥቂቱ........................................ 50

## የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

## ይድረስ ከመጽሐፌ አንባብቢዎች፤

፪ኛ /ተሰሎንቄ ፫/ ፲፯/

አጫጭር ታሪኮች በብዙ ሀገር ጸሐፊዎችና አንባቢዎች ዘንድ የተለመዱና የተወደዱ ናቸው፤ እኔውም ብሆን እኔው እራሴ በዚችው ባለችኝ ጭንቅላቴ አጭር ታሪክ ማንበቡ ደስ ይለኛል። ለምን እንደሆነም ይገባኛል።

ይቺን መጽሐፌን ስጽፋት ተጨንቄአለሁ፤ አጨናነቁ ላሳምራት ላስቀረቅርት ብዬ አይደለም። ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጐረቤቱ አይኖርምና እንደ ጭንቅላቴ እጽፋለሁ ብዬ ቆርጬ ነው የተነሣሁት።

ይተጨነቅሁት እያንዳንዱ ታሪክ ይረዝምና ስልቹ አንባቢዎች ያስለችብኝ ይሆን? ያጥርና ያሳቅቅቸው ይሆን? አይጥማቸው ይሆን? እያልኩ ነው፤ አሁንም አላወቅሁትም፤ የምታውቁት እናንተ ወይም እርሶ ራስዎ አንባቢው ነዎት።

አንዳንዶች «ጥሩ የምክር መጽሐፍ ለምን አትጽፍም» ይሉኛል፤ እውነታቸውን ነው፤ ግን ደግሞ የማምንበት አንድ ዓላማ አለኝ፤ ልጅ ነኝ ብዬ ባልመካም በሠላሳ ዓመት ዕድሜዬ ምን ብዬ ማንን ነው የምመክረው? ከዚህ ከጮርቃ አእምሮ የሚፈልቀው ምክርስ ማንን ነው የሚጠቅመው?

ሳላር ስበስል ብጽፈው ያምርበኛል፤ ተርፎ ከሚቀር ዕድሜ አይንፈገኝ የምጽፈው ብዙ አለኝ።

ይቺ መጽሐፌ የውሸት አጻጻፍ ናት፤ ልብ ወለድ ናት ማለቴ ነው፤ ታሪኮቹን ሁሉ ፈጠርኳቸው እንጂ ተፈጥረው አላገኘኋቸውም፤ እርግጥ አሁንም ደግሞ ውሸት እንዳላበዛ አንዳንድ በየሰው አፍ የሚነገሩትን ቀልዶች ጨምሬአለሁ።

እኔ ራሴ በተፈጥሮዬ ቀልድ የማላውቅ ሞዛዛ ችኮ ቢጤ ስለሆንኩ የመጽሐፍቱ አቀላለድ የቸከ ደረቅ አቀላለድ ይሆንብኝ ይሆን ብዬ ሰግቻለሁ፤ ያላችሁትን በሉኝ እንጂ ሳልፈራ በድፍረት አቅርቤላችኋለሁ።

«ይምስለ አይምስለ የጠይብ እጅ ከከሰል» እንደሚባለው እጄ እንደልማድ ሆኖበት መሞጫጨርን ይወዳል፤ ያን ሚጫራዬን ደግሞ ካነበብኩ ቀጄ መጣል ነው፤ ይሰለቸኛል፤ እጠላዋለሁ፤ ስለዚህ አንድ ጊዜ በማርቀቅ የጻፍኳትን እንድትታተም አፈርድባታለሁ። ምናልባት አባጣ ጐባጣ ሆኖ አላስኬድ የሚል ገደላገደል ቢያጋጥማችሁ በደምዳሜ እመር እያላችሁ አላፉት።

የተራቀቀ የጽሑፍ አቀራረብ በመብራትም ብትፈልጉ አታገኙባት፤ የመንደር ወሬ አወራር ዓይነት ናት፤ ብዙ ጊዜ ከብዙ ሰው ጋር የማልገናኝ ሽጉራ ቢጤ ሆኜ ሳለሁ የመንደሩ ወሬ አወራር እንዴት አድርጌ እንዳጠናሁት እኔንም ገርሞኛል። ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ አንዳንድ ነገሮችን ስለነገረኝ ባለውለታዬ ነው።

በደህና እንክረም ከማለቴ በፊት ይቺን መጽሐፌን «ድብልቅልቅ» ያልኩበት ምክንያት የተደበላለቀ ታሪኮች ስላሉበት ነው ልላችሁ ፈለግሁ።

በደህና እንክረም።

# ሊቁ።

የተማረ ነው፤ አስቦ መመለስ ይችላል፤ ሳያስብ እንኳ የሚሰጠው መልስ ቅመም ነበርም ይሉታል፤ ይሔው የሕዝብ ውደሳ ነው ሽመልስን ሳያስበው ሊቅ አድርጎት ያስገኘው።

አንዳንድ ጓደኞቹ ዘመዶቹ በሙሉ ሊቁ ይሉት ስለ ነበረና አንዳንድ ነገርም ያደንቁለት ስለ ነበር ሽመልስ ጢሙን ማሳደግ ጀመረ፤ በዓይኑም ላይ ቀጭን ነጭ የሊቃውንት መነጥር ማድረግ ጀመረ።

በውነትም ሊቅ ነው፤ የሽመልስን ሊቅነት ማንም ቢሆን የሚመሰክርለት ነው። የሊቅነት ጉዞውን ከመያያዙ በፊትም የመሥሪያ ቤቱን ሒሳብ የያዘው እንደሆነ ማንም የለፋበትን ስንቱ አዋቂ ራሱን ያዞረበትን ሽመልስ ባንዴ ነው ቁጭ የሚያደርገው።

የመዝገብ አያያዙም ቢሆን ሽመልስ ወዲያ የተባለለት ነው፤ አለቃው ሽመልስን እንድወንድማቸው ነበር የሚያዩት እንዲ እንደአለቃቅው አልነበሩም፤ ወይም በሌላ አነጋገር ሽመልስን እንደ አለቃ ያዩት ነበር እንጂ አለቃ ነኝ ብለው አያበሳጩትም ነበር። ይኸ ሁሉ ታዲያ በሥራው ነው እንጂ ሽመልስ በተፈጥሮው ኩሩ ስለሆነ እጅ ነስቼ ተለማምጨ የሚባል ነገር አያውቅም ነበር።

እናቱ የሞቱት ሽመልስ ገና ከስምንተኛ ክፍል ሆኖ ነው፤ እናቱ በሞቱ ባመታቸው ነው ሽመልስ ሽማግሌ አባቱን ለመርዳት ብሎ ሥራ የያዘው።

አጎቱ አቶ ለማ ከልጅነቱ ጀምረው ሽመልስን ተንከባክበው ይዘውት ነበርና በኋላ በጣም ይወዱታል፤ አቶ ለማ መሐን ስለሆኑ ላለ ሀብታቸው ወራሼ ቀራሼ ሽመልስ ነው ብለው በቁማቸው ተናዘውለታል።

ሽመልስ ሥራ ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ሽማግሌ አባቱ የልጄን ደስታ ባይኔ ልየው እያሉ ልጃቸው ሚስት እንዲያገባ ፈልገው ነበር፤ ሽመልስ ገና ነኝ ልደላደል ትምህርቴንም ውጥኔንም ላገባደው እያለ እንቢ ብሏቸዋል፤ ሽማግሌ አባቱም ጧትና ማታ በየቤተ ክርስቲያኑ እየሮጡ ፈጣሪዬ እባክህ ልጄን ውሀ አጣጪውን አጋጥመው እያሉ ይጸልዩለታል።

የሽመልስ አባት ስለ ሽመለስ ማግባት የሚጨነቁት አንድ ልጃቸው ስለሆነ ፍሬ እንዲተካላቸው እንጂ ሽመልስ ባለጌ ወይም አሳሳቢ በዋለበት የሚያድር ሆኖ አይደለም። ጨዋ ነው፤ ከቤት ሲገባም ከመጽሐፍ ጋር መታገል ነው፤ ሲበላ እንኳ መጽሐፉን አምኖ አይለየውም።

አባቱ የልጇን ደስታ እንዳሉ ሚስታቸው እመት ልኬለሽ በሞቱ በአራተኛ ዓመት የልጃቸውን ደስታ ሳያዩ ሞት ቀደማቸው፤ ነገሩን እንጃ እንጂ በፍርድ ነው የሞቱት፤ ሽመልስ አባቱን በጣም ይወድ ነበርና እጅግ አድርጎ አዘነላቸው ይባላል።

የሽመልስ ሊቅነት ይታወቀና የለየለት አባቱ በሞቱ በሁለተኛው ዓመት ነው። ያኔ ነው ጢሙን ማሳደግና ነጭ መነጥር ማድረግ የጀመረው፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው በሕዝብ አፍ መወደስ የጀመረው።

ሽመልስ ከወርዋ ጭራ እወርዋ ቀንድ ድረስ ከሥራ መግባቱን ተወ፤ ፒፓውን ይለጉምና ዶለዝ ከዘራውን ይይዝና ጠጉሩን ያንጨፈርርና ቀጥ ግትር ድርቅ ብሎ በአራዳው መሐል መዞርን ጀመረ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው አቶ ለማ ሽመልስን አብዷል ያሉት፤ እንዲታሠርላቸው ለፖሊስም አመልክተው ነበር፤ ፖሊሶቹን ግን የሽመልስን ሊቅነቱን እንጂ አለማበዱን አረጋግጠው የአቶ ለማን ሐሳብ አልሞሉላቸውም።

ሽመልስ ርቆ ነው የሚያስበው፤ እጅግ በጣም ብዙ ርቋል፤ አንዳንዴ ከትርያኖን ቡና ቤት በራፍ ላይ ይቀመጥና አንገቱን ቶሎ አይመለስም፤ ባንድ በማይታወቅ ሚስጢር ይጫወታል፤ ሌላውን ሊገባው የማይችል ምርምር ይመራመራል።

ከየቡና ቤቱ በር ይቀመጥና ሲያስብ በአጠገቡ ከበውት «ነገ የሚወጣ ሎተሪ ይግዙ፤ ጥሩ ምላጭ፤ ናሳምር፤ ንቦርሽ? ምን ይምጣሎት?» የሚሉትን ሁሉ አይሰማም።

ብዙዎቹ ዘንድ ሽመልስ አንድ ጥሩ ፈላስፋ እንደተገኘ ተቆጠረ፤ ዕድል አግኝተው ወይም አጋጥሟቸው ከሽመልስ ጋር የተነጋገሩ ሁሉ ስለ ሽመልስ ይደነቁ ነበር፤ አንዳንዶቹ አዬ ጉድ እንዲህ ይበላሽ አያሉት ያልፉ ጀመር።

አንድ ቀን ወደ ማታ ገደማ ከስድስት ኪሎ ካለው መናፈሻ ብሔድ ሽመልስ ካንድ ዛፍ ሥር ካለ የድንጋይ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ሲያነብ አገኘሁት።

እንዲያንጋግረኝ ብሞክር እያየኝ ዝም አለኝ፤ በሐሳብ መመሰጡ ገባኝና አላውከውም ብዬ ሽርሽሬን ቀጠልሁ፤ ጥቂት ተዘዋወርሁና ተመልሼ ከሽመልስ አጠገብ ስመጣ አሁንም ሽመልስ ሲያስብና ሲያሰላስል አገኘሁት።

መዞሩ ደክሞኝ ነበርና ካጠገቡ ቀስ ብዬ ቁጭ አልኩ፤ ጥቂት ቆይቶ «ታዲያስ» አለኝ።

«አለሁታ» አልኩትና «ለምን ሥራን ተውክ?» አልኩት።

«ተውኩ» አለኝ

«ለምን?» አልኩት፤

«እሠራለሁ አልተውኩም» አለኝ፤

«የት?»

«ከዚህም» አለኝ

«ከዚህ ምን ትሠራለህ?» አልኩት፤

«እመራመራለሁ» አለኝ፤

«እየተመራመሩ የሚለብሱትንና የሚቀምሱትን ማግኘት ያስፈልጋል» ብለው ሽመልስ ከዘራውን ተመርኩስዞ በሩቁ እያየ «እንደኔ አባት እኮ አዋቂና ታላቅ ሰው አልነበረም» አለኝ።

«እንዴት?» አልኩት፤

«በምን እንደሚሞትና የሚሞትበትንም ቀን ለይቶ ያውቀው ነበር» አለኝ፤

«ነቢይነት ወይስ ወልይነት ነበራቸው?» ብለው

«አይደለም» አለኝ፤

«እንግዲያ እንዴት ሊቃውቁት ቻሉ» አልኩት፤

«ሰኔ ፳ ቀን በስቅላት እንዲሞት ተፈርዶበት ስለ ነበር ነው» አለኝና እንደ ፈዘዘ ቀረ።

ሲጃራውን አንድ ሁለቴ ምጎ ጭሱን አቦነነና «የሚገርመኝ አንድ ትልቅ ነገር አለ» አለኝ፤ እግሬን አነባብሬ እድንጋዩዋ ወንበር ላይ እንደተቀመጥሁ «ምንድነው እሱ?» አልኩት» ይኸ ሕዝብ ለሀብት ብቻ የሚስገበገብ አውሬ ሕዝብ ነው» አለኝ፤

«አዎ» አልኩትና «ሀብት እኮ እጅግ በጣመረ ጥሩ ነገር ነው» ብለው ከፊቴ ቆም አለና በሚያሽሚጥጥ ዓይኑ እያየኝ «ስለ ሀብት ምን ታውቃለህ?» አለኝና እግሩ ሥር የነበረችውን ድንጋይ በእግሩ ከነባበለና ቀስ እያለ መንጎራደድ ጀመረ።

ካቅሜ በላይ ተነፈስሁና «ሀብት ካለህ እንደ ልብህ ትሆናለህ፤ እንዳስፈለገህ ትሠራለህ፤ እንደተመኘኸው» ስል አቋረጠኝና «ተወኝ ጠባብ አስተያየትህን፤ ባድናቆት ይሻለኛል፤» አለኝና «እኔ አንድ ጊዜ የሆንኩትን ታውቃለህ?» አለኝ።

«ድሬደዋ ልወርድ በባቡር ተሳፈርኩ፤ ለሣጥኔ አልከፈኩም ነበር፤ ውልንጪቲን እንዳለፍን አንድ የባቡር ዘበኛ መጣና ይህ ትልቅ ሳጥን ሊከፈልበት ይገባል አለ።

«መልስ የሚሰጠው ስላጣ የማነው? ብሎ ጮኸ፤ ዝም አልነው፤ እኔም ሁኔታውን እየታዘብሁ ዝም አልኩት፤ ዘበኛው እንደ ገና ጮኸ፤ የኔ ነው አልኩት ይክፈሉ አለኝ፤ ገንዘብ አልያዝኩም ነበርና የምከፍለው የለኝም አልኩት።

«ሳጥኔን ሊጥል ጎተተው፤ ሳጥኔን ይገፔ ወደ ኋላ ጎተትሁ፤ በኋላም የሚያደርገውን ልይ ብዬ ለቀቅ ባደርግለት አሽቀንጥሮ ጣለው፤ እንደሚመስለኝ እንጃግራንጃዬ አሰልችቶት ይሆናል።

«በሳጥኔ መውደቅ በጣም አዘንሁ፤ ጭው ካለው በረሃ፤ እንኳን የሰው ዘር የወፍ ዘር በሌለበት ዱር ነበር ሳጥኔን የጣለው» አለና ፍዝዝ ብሎ ባንድ አቅጣጫ አተኩሮ እያየ ቆመ።

«ታዲያ ስለሀብት ያለህ ፍልስፍና ይሔ ነው?» በልው ከፈዘዘበት ሐሳቡ ተመለሰና ካጠገቡ አንድ ቅጠል ቀንጠብ አድርጎ እንደ ገና ወደ ፊቱ በረቀቀ አስተያየት እያየ «እኔ ሳጥኔነ ከድሬዳዋ ባላገኘው ኖሮ እነሱ ግን ስለገንዘብ የነበራቸው ጉጉት የሚያገርም ነው» አለኝ።

«በረሃ ነው ዱር ንወ ብለሃል፤ እንዴት ሳጥኑን አገኘኸው? እንዴትስ ድሬድዋ ድረስ መጣልህ? ወይስ ደግሞ ባቡርን አስቁመህን ወርደህ ነው ያመጣኸው?» ብለው እንዳዘነና እንደ ተከዘ «አይደለም፤ አይደለም ወዳጄ» አለኝ።

«ታዲያ እንዴት ነው?» አልኩት፤

«በምሥጢር ነው፤ የድብቅ ዕቃ ነው?» አለኝ፤

«ኮንትሮባንድ ነው?» ብለው፤

«ነው፤ ሳይሆንም አይቀር» አለኝ።

«ኮንትሮባንዱስ ምንድነው? ሳጥንህን ያመጣልህ ማነው?» አልኩት፤

«አንዲት ጨሎ ናት» አለ።

«ዘበኞች» አለኝ፤

«የምን ዘበኞች?» ብለው፤

«የባቡሩ» አለኝ፤

«እንዴት?» ብለው

«ጨሎዋ ገንዘብ አልከፈለችም ነበር፤ ደብቀኝ ብትለኝ ሳጥኔው ውስጥ ደበቅኋት ሳጥኔን ሲጥሉ ጨሎዋ ከውስጡ እንዳለች አብረው ነው የጣሏት፤ እሷ ነች ሳጥኔን

ይዛልኝ ድሬዳዋ ድረስ የመጣችው፤ አየህ ለሠራሁለት ውለታ ሲሸቅል ከርሞ የመለሰውን ወሮታ» አለኝ።

ሳቅሁበት፤ «ሳታመዛዝን አትሳቅ» አለኝና «በዚህ ዓለም ላይ ስንት አስደናቂ ነገር ያለ ይመስልሃል?» ብሎ ከአጠገቤ እያዘነ ቆም አለ።

«አዎ አለ» አልኩት፤

«ለምን አለ? አለኝ፤

«ለምሳሌ ከሚያስደንቁኝ መሐል አንዱ ያንተ ነው» አልኩት፤

«ፍልስፍናዬ ወይስ ምኔ?» አለኝ፤

«ምንህም ያስደንቀኛል» አልኩት፤

«እንደሌሎቹ አንምተ እንደእብድ ታስበኛለህ» አለኝ።

«አላስብህም» ብለው፤

«ታዲያስ? አለኝ፤

«ሊቅ ነህ» አልኩት፤

«አበድክ ይሉኛል» አለኝ፤

«አይዞህ፤ አይክፋህ ዲዎጋንም በዘመኑ እብድ ይባል ነበር፤ በፍልስፍና ጥናትህ በርታበት» ብለው ሽመልስ ሳቅ አለና «ከዶሮ ጭንቅላት የሚሻል ናላ አለህ» አለኝና

«ስማ ሲጃራ ማጨስን ለመተው ዘዴው በጣም ቀላል ነው» አለኝ።

የሲጃራ ሱስ የሚያጠናብረኝ ሰው ነበርኩና የመተውያውን ዘዴ ለማግኘት ጓጉቼ «እንዴት ነው ዘዴው?» ብለው «እኔ ለምሳሌ መቶ ጊዜ ትቻለሁ» አለኝ። «ታዲያ ይሔ አሁን የያዝከው ሲጃራ አይደለሞይ? ከተገናኘን ጀምሮ ሦስት አራቴ አቀጣጥለሃል፤ መተው ማለት የቱ ነው?» ብለው «አዋቂ እንህ በማለቴ ተሳስቻለሁና ይቅርታ አድርገልኝ» አለኝ

«እንዴት?» አልኩት፤

«ተወው ነገሩ አልቋል» አለኝ፤

«እኮ እንዴት?» ብለው፤

«መቶ ጊዜ ትቻለሁ ማለት አሁንም አልተውኩም ማለት ነው፤ መተው አንዴ ነው» አለኝና ከተቀመጠበት ተነሥቶ ይንጎራደድ ጀመር።

ሽመልስ በእርግጥ የፍልስፍናን ምርምር የያዘ ሰው ነው አልኩ፤ ከኛ የተለየ ነገርና ሐሳብ ስለሚያመጣ ሰዎቹ ያበደ መስሏቸው ይሆን? ወይስ በአካባቢው አለ ማወቅ ይሆን እንደ ዕብድ የተቆጠረው? እያልኩ ሳስብ ሽመልስ እጆቹን ከወደኋላው ደራርቦ ከፊቴ እየተንጐራደደ «ስማኝ አንዴ» አለኝ።

«በጄ አልኩ፤

«ድሮ ወታደር ነበርኩ፤ ባንድ ጦር ሜዳ ላይ ዘምቻለሁ፤ በጦሩ ሰፈር ለሁለት ወር ቆየሁ፤ በኋላ ሚስቴ ናፈቀችኝ፤ ከአዛዣችን ዘንድ ቀርቤ ሚስቴ ናፍቃኛለችና ፈቃድ ተሰጥቶኝ ወደ ከተማ ልመለስ አልኩት፤ አዛዣችን ትኩር ብሎ ተመለከተኝና ሕዝቡ ሁይሉ ለሀገሩ ሲያስብ አንተ እንዴት ለሚስትህ ታስባለህ? አለኝ።

በሚፈለግብኝ የወታደር ሥነ ሥርዓት ቆሜ ኮሎኔል እኔነም ፈቃድ ያስጠየቀኝ ይሔው ነው አልኩት ኮሎኔል እዛፍዋ ሥር እንደ ቆመ ቀና ብሎ አየኝና እንዴት? አለኝ፤ ለሚስቴ የማስብላት እኔ ብቻ ስለሆንኩ ነው አልኩት፤ ባንተ ሐሳብስ አመላለሴ ምን ይመስልሃል?» አለኝና ሽመልስ ቆም ብሎ ተመልክቶኝ እንደ ገና በዝግታ ይንጎራደድ ጀመር።

ሽመልስ የጠየቀኝን መልስ ብሰጥ እንደገና ደግሞ ችሎታዬን በሱ ዘንድ ማስገመት ይሆንብኛል ብዬ በጠቅላላው «ሁሉም በወግ ነው» ብዬ መለስኩለት።

ሽመልስ ተክዞ የጠለቀችው የማታይቱ ጀንበር የጋመችውን አየር እየሞቀና በአበባዎቹ መሐል እየተንጎራደደ ለጥቂት ጊዜ ቆየና «ታውቃለህ አንድ ጊዜ የሆንኩትን» አለኝ።

«ምን ሆንክ?» አልኩት፤

«ያባቴ አንድ ቁራጭ መሬት ነበረችኝ፤ ከወረስኳት በኋላ ባላንጣ ተነስቶብኝ ከሰሰኝ፤ በቀጠሮ ብዙ ተጉላላሁ፤ ከጠበቃዬ ጋር ተማከርንና ሁለት መቶ ብር ጉቦ ቢጤ ለዳኛው ሰጠሁት፤ በቀጠሮው ቀን ዳኛው ፈረደብኝ።

«ያንለታውኑ ማታ ከጠበቃዬ ጋር ከዳኛው ቤት ሔድን፤ ለምን እንደፈረደብኝ ጠየቅነው፤ ዳኛው ሲነግረኝ ባላንጣህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር ሰጥቶኝ ነበር፤ እኔ ግን በማግሥቱ ሃምሳነው ብር ለባላንጣህ መለስኩለት ነገሩን እንዳጠናሁት ያ መሬት ለባላንጣህ የሚገባ ስለመሰለኝ ነው የፈረኩብህ፤ አለኝና ሔድን፤ ባንተ አስተያየት ዳኛው ጥፋተኛ ነው አይደለም? አለኝ።

«ዳኛው ጥፋተኛ ነው» አልኩ

«እንዴት?» አለኝ፤

«ከበፊቱ ባልተቀበለህ፤ ከተቀበለህ ወዲያ ደግሞ ሊፈርድልህ ይገባው ነበር» አልኩት።

«ተሳሳትክ» አለኝ፤

«እንዴት?» አልኩት፤

«ዳኛው አዋቂ ሰው ነው፤ ከሁለታችንም እኩል ገንዘብ መቀበሉ በትክክል ለመፍረድ ነው፤ በአስተአይየቱ ፍርድን አላዛባም፤ ጥቅሙንም አላጣም፤ ይኸወልህ ይህን የመሳሰሉ አዋቂዎች በሀገራችን ሞተዋል» አለኝ።

«ታዲያ አንተ ይግባኝ አላልክምን? ብለው፤

«የዳኛው አዋቂነት ተስማምቶ ስለገባኝ ይግባኝ አላልኩም» አለኝ።

«እንግዲህ ሽመልስ ብርድ ተነሣ» አልኩትና ከተቀመጥኩበት ብድግ ስል «እንሒድ ማለትህ ነው?»

አለኝ «አዎ» አልኩትና እያዘገምን ቁልቁል ወረድን።

መንገድ ለመንገድ እያወራን ስንሔድ አንድ እግሩ ተቆርጦበት በእንጨት ላይ ዡል እያለ የሚሔድ ሰው አጋጥሞን ምፅዋት ለመነን፤ አምስት ሳንቲም ሰጠሁትና አለፍን «ደግ አረግህ» አለኝ ሽመልስ።

«ምኑን» አልኩት፤

«መመጽወቱን» አለኝና «ዛሬ ጧት በመንገድ ሳልፍ አንድ ጠረንገሎ ምጽዋት ለመነኝም ቆም ብዬ ሁኔታውን ባየው ፍጹም ጤነኛ ነው። ነደደኝና እንዲህ ጤነኛ ሆነህ ለምን ትለምናለህ ብለው ለማኙ ሲመልስልኝ ምን እንዳለኝ ታውቃለህ? ጌታዬ ሳለምን የወሰድኩትማ ስድስት ወር አሳሰረኝ ቢለኝ ተገርሜ አለፍኩት አያስገርምህም?» አለኝ።

«እንዴት ነው ሳይለምን የወሰደው?» ብለው፤

«ሰርቆ ነዋ!» አለኝ።

ከሚያዝያ ፳፯ አደባባይ (፬ ኪሎ ድረስ) ደርሰን ከመብርትዋ ሥር ቆም ብለን ስንለያይ «ለመሆኑ አባትህ ደኅና ናቸው?» አለኝ። «ምነው እሳቸውማ ከሞቱ ቆይተው የለ» ብለው «ይቅርታ ተሳስቼ ነው፤ መሞታቸውን አውቃለሁ ዛሬም እዚያው እመቃብራቸው ውስጥ ነወይ ያሉት ማለቴ ነው» አለኝና ተሰናብቶኝ ሄደ፤

እነኝህ ሊቆች አንዳንዴ ይቀባዥራሉ እንዴ! አያልኩ እኔም ወደ ቤቴ ሄድሁ።

አንድ ቀን አጎቴ አቶ ለማ አገኙኝና «አባክህ ሽመልስን ወደ ጠበል ወይም ወደ ሐኪም እንውሰደው» አሉኝ» «ምን ሆነና» ብላቸው «አብዷል» አሉኝ። «የለም አላበደም፤ በኔ አስተያየት ሽመልስ ለመመራመር ብሎ እንዳልነበር ሆነ እንጂ እብድ አይደለም» አልኳቸው።

«ለይቶለት እየቀባጠረ!» አሉኝ።

«ምን አጠፋ? ፍልስፍናውን ይሆናል ቀባጠረ የምትሉት» ብላቸው «የለም ለይቶለታል» አሉኝና «በቀደም ከፎቅ ላይ ወድቆ» ሲሉኝ ደነገጥሁና ጉንጮቼን በእጆቼ ይዤ «ከየትኛው ፎቅ?» ብላቸው፤ «ከአዛዥ ተፈሪ» ብለውኝ ወዲያው በመቀጠል «ሰው ሁሉ ተደናግጦ ተሰበሰብና እንዲጠጣው ውሀ በብርጭቆ ቢሰጡት አንድ ብርጭቆ ውስኪ ለማግኘት ከስንተኛው ፎቅ ላይ መውደቅ ያስፈልግ ኖርዋል» አለ፤ ታዲያ እንዲህ ዓይነቱን ነው አላበደም የምትለው» አሉኝ።

«አላበደም» አልኳቸው። «ምን መሆንህ ነው?» ብለው ተቆጡ። «የለም አይቆጡ፤ ሽመልስ የዚያን ጊዜ አንድ ሐሳብ ይዞት ሳያስበው ይሆናል የወደቀው ምናልባትም ስለ ውስኪ ያስብ ይሆናል፤ ስለዚህ በማናውቀው ነገር አንፍረድ ሽመልስንም እንደ ዕብድ አይቁጠሩት» አላቸው፤ ሳናስበው ሽመልስ ከመሐላችን ተደባለቀ።

ዝም ብሎን በመደባለቁ አቶ ለማ «ያውልህ እንግዲህ አሁንም አታምንም?» አሉኝ። «አላምንም» አልኳቸው። «ሰው ከሰው ሲገናኝ እንደላም ከተቀላቀለ ወዲያ ሰው ብቻውን ካወራ ወዲያ ብቻውን ሆኖ የሚታዩኝ ነገሮች አሉ እያለ ከነሱ ጋር ከተነጋገረ ወዲያ ጤናማ ይባላል?» አሉኝ። «እንዲህ ይላላ እንዴ?» ብላቸው፤ «አትጠይቀውም?» አሉኝ።

ወደ ሽመልስ ዞር አልኩና «ሽመልስ? አንድ ክፍል ውስጥ ብቻህን ስትሆን ካጠገብህ ሰው ሳይኖር ድምፅ ይሰማሃል?» ብለው «አዎ! ውሾችም ዶሮዎችም ከሩቁ ሲጮሁ እሰማለሁ» አለኝ።

የኮቱን ኮሌታ እየነቃቀስኩለት «ምንም ዓይነት ድምፅ ከማይሰማበት ጭር ካለ ቦታ ካንድ ክፍል ቤት ውስጥ ሲዘጋብህስ?» ብለው፤ «አዎ! ይሰማኛል» አለኝ

ደነገጥ አልኩና «እንዴት ዓይነት ድምፅ ይሰማሃል?» ብለው፤ «የሰው ንግግር» አለኝ። «ከየት የመጣ ድምፅ ይመስልሃል የሚሰማህ?» ብለው፤ «ስልክ ይጮሃል ሳነሳው የማላየው ሰው ማን ልበል ጌታዬ ይለኛል» አለንና ተለየን።

አቶ ለማ ስለ ማበዱ፤ እኔ ሰለ ማበዱ ጥቂት ተከራከርን። በፍልስፍና ዓለም ውስጥ ያሉ ሰዎች እንደዚሁ መሆናቸውን ገለጽኩላቸው። አቶ ለማ ግን «በየትኛው ጭንቅላት ነው የሚፈለሰፈው? ማበዱ ነው! ያኑ አጀማመሩ ወፈፌነት ነው» አሉኝ።

በምንም ዓይነት መንገድ ባስረዳቸው ሽበቶው አቶ ለማ ፈጽመው የማይሰሙኝ ሆኑ። እስተነአካቴው «ተወኝ ይህን የማይረባ ፈሊጣችሁን! ኧረ ሊቅነት እንዲህ አይደለም! ኧረ ስንት ሊቆች የፈለቁበት አገር ናት ስንቶቹን አይተናል! ተወኝ የናንተን ፈላስፋነት!» አሉኝ።

ካቶ ለማ ጋር ብዙ ተከራከርን። ሽመልስ ለማበዱ ብዙ ማስረጃ ማግኘታቸውን ነገሩኝ። በመጨረሻው ከቤታቸው አብረን እንድንሄድና የሽመልስን ማበድ በማስረጃ ሊያስረዱኝ ፈለጉ። በዚሁ ተስማምተን ካቶ ለማ ቤት ሔድን።

ካቶ ለማ ቤት ሆነን ሽመልስን ስለምንፈትንበት ጉዳይ ተማከርንና ሽመልስን ጠራነው። ወዲያውኑ አንድ መዶሻና ሚስማር ሰጠነው ሚስማርዋን ከግድግዳው ላይ እንዲመታት ነገርነው። ሽመልስ «እናንተ የሌላ ጉልበት የሚጥማችሁ!» አለንና ሚስማርና መዶሻውን ይዞ ወደ ግድግዳው ሔደ።

አትኩረን ስንመለከተው የሚስማርዋን ጠፍጣፋ ጫፍ ወይም ጭንቅላትዋን ከግድግዳው ላይ አድርጎ ሹልዋን ወደ መዶሻው መምቻ አደረገ፤ ይህን ስናይ አቶ ለማ ጐንተል አደረጉኝ፤ እኔም ቀስ ብዬ በጆሮአቸው «እውነትም ራሱ ዞርዋል» ብላቸው «ራሱማ በመዞሩ ነው ሚስማሩን ያዞረው» ብለው ሹክ አሉኝ።

ሽመልስ ጥቂት አሰበና ወደ ኋላው ዞር ብሎ ሚስማሩን ከግድግዳው ላይ ሳያነሳ የኋላውን ግድግዳ አየ፤ ወዲያውኑ «ይህ ሚስማር የተሠራው ለወዲያኛው ግድግዳ ነው» አለና ከወደ ጀርባው ወደ ነበረው ግድግዳ ሚስማሩን እንደያዘ ሔዶ በሚገባ በደንብ ሊከነችረው ሲል አቶ ለማ ግድግዳቸው እንዳይበላሽ ተወው ይቅር ብለው መዶሻውን ተቀበሉት።

«ይሔውሎት አለበደም» ብላቸው «ወይድልኝ ወዲያ፤ አሁንስ አንተም አብደሃል፤ አሁን ሽመልስን ነው አላበደም የምትለው? ጨርቁን መጣል ነው የቀረው፤ ይልቅስ ነገ ናና ከሐኪም ቤት እናስመረምረው» አሉኝና እሺ ብያቸው ሔድሁ።

ሌሊቱኑ ስለ ሽመልስ ሳስብ አደርሁ፤ አሁን ምን ቸገራቸው ባያበሳጩት? ለምንስ እብድ እብድ ይሉታል? ለምንስ ሐሳቡን ያሰናክሉታል? ለምንስ እንደ ፍላጎቱ አይፈፅሙለትም? ታዲያ ገና ብቅ ሲሉ አበዱ እያልን ካሳበድናቸው ምን ተስፋ አለ? አሁን ሽመልስ ምኑ ነው የማበዱ ምልክት? ጥሩ፤ አሁን ሐኪሙ አትንኩት አክብራችሁ ያዙት ሲላቸው ይረዱት የለ? አዎ ሐኪሙ ያውቃል ይነግራቸዋል፤ ፍጹም ያላበደ ፈላስፋ ነው ሲላቸው ያርፉታል ስል አደርኩ።

በነጋታው አቶ ለማና እኔ ሽመልስን ይዘነው ከአእምሮ ሐኪም ዘንድ ወሰድነው፤ ሐኪሙ የምርመራ ሥራውን እንደ ጀመረ ሽመልስ ሐኪሙን «እስቲ አንድ ሲጃራ

ይስጡኝ» አለው፤ ሐኪሙም የሚመጣትን ሲጃራ ከመኩስትሪያው ላይ አጠፋና ከሲጃራ ፓኬቱ አንዱን ሲጃራ አውጥቶ ለሽመልስ ሰጠው።

ከሽመልስ የሲጃራውን ወረቀት ተረተረና ትንባሆንው በእጁ ላይ አድርጎ ባንደኛ እጁ እየቆነጠረ አፍንጫው ውስጥ ጨምሮ ደመደመው፤ አተኩሮ ይመለከተው የነበረው ሐኪም ራሱን ነቀነቀና «በውነቱ ልረዳህ የሚገባኝ ሰው ነኝ» አለው።

ሽመልስም ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ከፊቱ የቆመውን ሐኪም አሻቅቦ ትኩር ብሎ እየተመለከተ «አዎ ዶክተር ሊረዱኝ ይገባልና በክብሪት ያያይዙልኝ» አለው።

# እምብየ።

ወይዘሮ ደብሪቱ አቶ ካብትህ ይመር ለብዙ ጊዜ ባበልና ሚስትነት አብረው ኖረዋል፤ በመንደራቸው በአካባቢያቸው ሕዝብ ዘንድ በጠባያቸውና በማንኛውም ተግባራቸው ተወደውና ተከብረው ይኖራሉ።

አንድ ልጅ ነው ያላቸው፤ ወይዘሮ ደብሪቱ ገና በኮረዳነታቸው ጊዜ ከእኝሁ ካቶ ካብትህ ይመር የወለዷት ሴት ልጃቸው ከሞተች በኋላ የወር እልፊት እንኳ ሳይውቃቸው ኖረዋል፤ እንደሚወራው ልጃቸው የሞተች ጊዜ በጣም አዝነው ልጃቸውን ላስቀብር ብለው በመቃብሩ ላይ ሲንከባለሉ ያኔ ነው አሉ ማኅጸናቸውን የተጠናወታቸው።

በእስተእርጅና ጊዜያቸው የወይዘሮ ደብሪቱ ጠጉር ገብስማ፤ ያቶ ካብትህ ይመር ጠጉር ንድፍ ጥጥ በመሰለበት ዘመን ነው ያሁኑን ልጃቸውን አድማሱን የወለዱት።

ቢሆንም አቶ ካብትህ ይመር የሚኒሊክ ዘመን ጎረምሳ ወይዘሮ ደብሪቱ የዘውዲቱ ጊዜ ኮረዳ ስለ ነበሩ ያኔ የበሉት ጮማ የዛሬውን የእርጅና ጊዜ ቆዳቸውን ያወዛላቸዋል።

በስተእርጅና ያገኙትን አንድ ቅንጣት ልጃቸውን አድማሱን አንከባክበው አሳደጉት፤ በመብልና በልብስ አይጎዳ እንጂ አቶ ካብትህ ይመር ቀጥ አርገው ይቀጡታል፤ አቶ ካብትህ ይመር አንኳን የራሳቸውን ልጅ የጎረቤትም ቢሆን ሲማግጥ ሲባልግ የማይወዱ ናቸው፤ የማንም ልጅ ቀጪ ናቸው።

አድማሱንም ደህና አድርገው እየቀጠቀጡና እየቀጡ አሳድገውታል፤ ሲገርፉት ሲመቱት የወለዱት አይመስሉም፤ ይልቅስ ወይዘሮ ደብሪቱ ገርና የዋህ በመሆናቸው በአንድ ልጃቸው በአድማሱ የማይጨክኑት እሳቸው ነበሩ፤ ካቶ ካብትህ ይመር ጋርም ሁልጊዜ የሚፋጁት በዚሁ በስተእርጅና ባገኙት ባንድ ቅንጣት ልጃቸው ነው።

ወይዘሮ ደብሪቱ «የተባረከ የተቀደሰ ልጅ ስጠኝ ማለት ነው እንጂ እግዜር ያልባረከውን ዱላ አይመልሰውም» የሚሉት ዘዬ ስላላቸው ይሄንኑ ሁል ጊዜ ላቶ ካብትህ ይመር ይነግሯቸዋል። አቶ ካብትህ ይመር ደግሞ «እግዚአብሔር እርዱኝ እረዳችኋለሁ ብሏልና ከኔ የተረፈውን እግዜር ያብጀው እንጂ መቅጣቴን አልተውም» ይላሉ።

ሆነ፤ አድማሱ እያደገ ሔደ፤ ጎረመሰ፤ ዓይነውሃው አላምር ስላላቸው አድማሱ በቶሎ ሚስት እንዲያገባ ፈለጉ፤ እውነታቸውን ነው፤ አዳምሱ ከሥራ አመሽሁ ጉዳይ አግኝቶኝ አመሸሁ እያለ ከበረሃም ከቁጭራም ከጣሊያን ሠፈርም ማመሻሸት ጀምሮ ነበር።

ለአድማሱ የታጨችለት ልጅ ሐረገ ወይን ናት፤ ሐረገ ወይን የባሻ አራምዴ የልጅ ልጅ ናት። ባሻ አራምዴ ከጎራው ገበየሁ ጋር አድዋ ዘምተው የሠሩት ጀብዱ በብዙ ይወራላቸዋል፤ በዱላ ዘምተው ሦስት ጠመንጃ ይዘው የተመለሱ ናቸው ይሏቸዋል።

ባሻ አራምዴ ዛሬ አርጅተው ከቤት ውለዋል፤ ዓይናቸው እርጅና ይከልለው እንጂ ልባቸው ብዙ ያያል የውለዷቸው ልጆች ብዙዎች ስለሆኑ ባሻ አራምዴ በሚገባ ተይዘው የሚጦሩ ናቸው። ስድስቱ ልጆቻቸው ቀድመዋቸው ባይሞቱባቸው ኖሮ ባሻ አራምዴ ዛሬ የአሥራ አራት ልጆች አባት ይሆኑ ነበር፤ ዓይናቸውንም የተተናኮላቸው ይሔው የልጆቻቸው ኀዘን ጠንቅ ሆኖ ነው ይባላል።

ባቶ ካብትህ ይመር በኩል ለአድማሱ የተደረገለት የጋብቻ ምርጫ ደስ የሚያሰኝና የሚያኮራ ነበር፤ ሁለት የምኒልክ ጊዜ ነፍጠኞች ሁለቱም ስለ አደዋ ያዩትን ለመናገር የሚችሉ ሁለቱም ስለ ጮማ አቆራረጥ ስለ ጠጅ አወራረድ ስለ ግብር አበላል ስለ ጉራዴ አስተታጠቅ አለ ጠመንጃ አያያዝ ስለ ፈረስ ግልቢያ አለ አሽከር ማሳመር ሊያወሩና ሊተርኩ የሚችሉ ሰዎች በጋብቻ መተሣሠር የሚያኮራቸው ነበር።

የአቶ ካብትህ ይመር ልጅ የልጅ ልጃቸውን መጫቱን ከሰሙ በኋላ ባሻ አራምዴ «ክብርህ ይስፋ ጸጋህ አይጓደል ዛሬን እንደ አብርሃም ዘር የምትጠብቅልኝ አምላክ የተባረክ ነህ» እያሉ በነግህና በምሽት ቁጣሮአቸው ያመሰግኑ ጀመር።

ዛሬ የሁለቱም ቤት አያወላዳም፤ ቅዳው ስጠ፤ ጣለው እረደው ቸአብላው ለማለት አልቻሉም፤ እንዲያውም እንዲህ አብላው ለማለት አልቻሉም፤ እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱን ነገር በሕልማቸው ቃዥተውት እንደባነኑ ቆጥረውታል፤ አንድ ሰው አንድ ሰሀንና አንድ እንጀራ ይዞ ብቻውን መብላት ከጀመረ ወዲህ ጊዜው ሞልቷል ብለዋል፤ ባሻ አራምዴማ የእምም ዘመን ብለውታል።

በልጆቻቸው ጋብቻ ከተስማሙ በኋላ ዘመኑ እንደሚፈቅደው ዓይነት ጋብቻ ልጆች እንዲተዋወቁና እንዲፈቃቀዱ ተባለ፤ በዚህ ጊዜ ነው ባሻ አራምዴ ብልጭ

ያለባቸው «ወይ ማርጀት ወይ እንደገና ልጅ ሆን አቅም ማጣት» አሉ ባሻ አራምዴ፤ «ወየው ደጉ ዘመን፤ ወየም የጨዋዎቹ ጊዜ እኔ ልኬለሽን ሳገባት ዓይንዋን ሳላይ ነው የጫጉላው እለት ነው ያወቅኋት፤ ኧረ የዕድሜ መርዘም እምኑ ላይ አደረሰኝ? ይሁን መቼም እንደ ጊዜው ነውና እንድፍጥርጥራቸው አሉ» አሉ።

ሐረገ ወይን ጠይም ናት፤ እንደአንዳንዶቹ አያስቀይምባትም እንጂ ቀጭን ናት፤ ታምራለች። የጥርስዋ ፍንጭት ለጠምነት ውበቷ አስዋቢዋ ነው። እንደ ሌሎቹ አብቻው የምትቅለበለብ አይደለችም። ረጋ በማለትዋ ተቀጥታ ማደጉዋንና የጨዋ ልጅነትዋን ትመሰክራለች። እስተነአካቴው ትመለኩሳለች ሲባልላት የኖረች ነች።

አድማሱም ቢሆን ራሱን የሚሸከምለት አንገት ያለው ነው። እርግጥ በደሞዙ ዝቅተኛ ነው የሚሉት ሴቶች አሉ። አድማሱ ግን ባላቸው ገቤው ቤቱን አሸንፎ ይኖራል እንጂ እንዳንዳዶቹ ከቤቱ ጋር ግብግብ ገጥሞ ፈጥኖ የወደቀ ያራዳ ልጅ አይደለም። ቢሆንም ታዲያ የአህያ ውሀ ጠጪ ነው እንጂ አመንዝራነት አያጣውም።

አድማሱና ሐረገ ወይን በግል እየተገናኙ ስለ ወደፊት ኑሮአቸው ይወያዩ ጀመር። በገፈርሳም በሾላም በኩል እየሄዱ እየተንሸራሸሩ ውለው ይመለሱ ጀመር።

ሐረገ ወይን የምትጠላው አግብቶ መፍታትን በመሆኑ በዚህ በኩል ያላትን ቅሬታ ለአድማሱ ነግራዋለች። አድማሱም እንደ እሷው መፍታት የማይወድ መሆኑን ነግሯታል። እንዲያውም የጋብቻ ውላቸውን በማዘጋጃ ቤት ሊፈጽሙ ተስማሙ። በማዘጋጃ ቤት ተዋውለን ከተፈራረምን መፋታት የለም ብለው ነው እውነታቸውን ነው፤ መፋታትን መጥላት ይገባቸዋል። ወላጆቻቸው ሳይቆርቡ እንደ ቆራቢ የኖሩ ናቸው። እነአድማሱም እንደ ወላጆቻቸው መሆን ፈልገው ነው በማዘጋጃ ቤት እንዋዋል ያሉት።

በየሣምንቱ እሁድ በሽርሽር ይውሉ ጀመር። ሐረገ ወይን ጨዋ ትሁን እንጂ ቅንጡ የጌታ ልጅ በመሆንዋ ምናልባት በትዳር ጊዜ ችግር ትፈጥርብኝ ይሆናል በማለት አድማሱ በእግርም በጋሪም ይዟት ይዞር ነበር። ደግሞም አንዳንድ የቀራት የአራዳ ቂንቂንነት እንዳያመልጣት ስለሚፈልግ፤ በየአራዳው ይዟት ሲንከራተትና ሲያስጠናት ከረመ። የአድማሱና የሐረገ ወይን ጋብቻ የተወሰነው የገብረ ወልድ ሕንፃ በተሠራበት ጊዜ በመሆኑ ትዝ ይለኛል።

የዚያን ጊዜ የገብረ ወልድ ሕንፃ ገና አዲስ መሠራቱ ነበር። ያን ጊዜ ሰማይ ጠቀስ ብለው ጋዜጦች ያወሩለት ሕንፃ ሁላችንም እያየን እንደምንደነቅበት ሁሉ አድማሱም ስለ ሕንፃው አሠራር ለማየት ሄዱ። ከሥሩ ቁመው አሻቅበው ሲመለከቱ፤ ገንቢዎቹ በተቀጣጠሉ አጣናዎች ላይ ሆነው ሲሠሩ አዩ።

አዳማሱ ስለ ሕንፃው ተገርሞ «ይገርማል!» አለ።

«በውነቱ በጣም ይገርማል! አየህልኝ የሰዎቹን ተንጠላጥሎ መሥራት?» አለች ሐረገ ወይን።

«አየሁት!» አለ አድማሱ።

«በውነቱ ይህን ዓይነቱ ሰዎች ተንጠላጥለው የሚሠሩት ሥራ በሕግ ሊከለከል ይገባል» አለች ሐረገ ወይን።

«ሰዎቹ በመወጣትና በመውረድ ይደክማሉ ብለሽ ነው ያሰብሽው?» አለና አድማሱ ሐረገ ወይንን ጠየቃት።

ሐረገ ወይን ለአድማሱ ጥያቄ ስትመልስ «ኖ አይደለም» አለችው። «ታዲያስ?» አላት አድማሱ። «እንዴ ምን ማለትህ ነው? አሁን እኛ በዚህ ከበታቻቸው ስናልፍ እላያችን ቢወድቁብንስ? » አለችው ሐረገ ወይን በኢዝህ ነው ጋብቻው የተወጠነው የገብረ ወልድ ሕንፃ ይሠራ በነበረበት ጊዜ መሆኑን የማስታውሰው።

የሐረገ ወይንና የአድማሱ ወላጆች ድል ያለው ድግስ ደግሰው አድማሱንና ሐረገ ወይንን በማዘጋጃ ቤት አዋውለው ዳሩዋቸው። እመት ዓመቴ «በዕድሜዬ ድግስ ያየሁት አንዴ ብቻ ነው» እያሉ እስከ ዛሬ ድረስ የሚያወሩት የያኔውን የሐረገ ወይንን ሠርግ ነው።

ሐረገ ወይን ወዲያውኑ ቅሪት ሆነች። ከስድስት ወር በኋላ አድማሱ ያቺን የድሮ ማምሸቱን ስለ ጀመረ አንድ መስቅል እንኳ ሳይተኩሱ ይነዛነዙ ጀመር።

አድማሱ ሐረገ ወይንን ያበሳጫታል። የሚያበሳጫትም እያመሸ ነው። ሐረገ ወይንም አድማሱን ለመቆጣጠርና ጠባዩን ለማስጣል ያህል በባለገ ቁጥር ትነዘንዘው፤ ትጨቀጭቀው ጀመር። በዚህ ምክንያት አድማሱ ሚስት ማግባት ወህኒ መግባት ነው ይል ጀመር።

ለጓደኞቹም ሁሉ ስለ ሚስቱ ጨቅጫቃነት ያወራ ጀመር። ግን ጠባዩን የሚያውቁት በትዳራቸው ላይ ጭቅጭቅ የፈጠረው እሱ እንጂ እሷ አለመሆንዋን ያውቃሉ።

አንድ ቀን አመሸና ገባ። ለምን አመሸህ? ብትለው «እንግዲህ ጀመርሽኝ!» ሰው ከጓደኞቹም ጋር ሲጫወት አያመሽ? እባክሽ ቅናትሽን በልኩ አድርጊው!» አላት። ሐረገ ወይን ሆድውና እንዳንዘረጠጠች ጠጋ አለችውና «ይቺ የየትኛው ጓደኛህ ጠጉር ናት?» ብላ ከኮቱ ትከሻ ላይ ረጅም የሴት ጠጉር አነሣችና እያሳየችው ጠየቀችው።

አድማሱ ከኮቱ ኮሌታ ግድም የተነሳችውን ጠገሩ ከሐረገ ወይን እጅ ተቀበለና እየሳበ ሲያይ «እኮ ተናገር» አለችው፤ አድማሱ ድንጋጤውን ውጦ «የፈረሱ ነዋ» አላት።

«የምን ፈረስ?» አለችው ሐረገ ወይን

«ቀን በጋሪ ስሔድ የደነበረው ነዋ» አላት አድማሱ

«ታዲያ የጋሪ ፈረስ ፋንዶ እንጂ ሸቶ ይቀባል?» ብትለው «አንቺ ሴት አትልከፊኝ ልተኛበት፤ ለራሴ ደከሞኛል» አለና እራቱን ሳይበላ አኩርፎ ተኛ።

በማግሥቱ ወደ ማዘጋጃ ቤት ሔዶ ከጋብቻ መዝጋቢው ሹም ዘንድ ቀርቦ እጅ ነሳ፤ ለምን እንደ መጣ ቢጠይቁት «አንድ ሰው» አለ አዳምሱ «አንድ ሰው በስህተት ሳያውቅ ተደናግሮ ገንዘብ የከፈለ እንደሆነ ይመለስለታል አይመለስለትም?» አላቸው።

ሹሙ ጠረጴዛቸውን ደገፍ ብለው እንደ ተቀመጡ ለአድማሱ «በሚገባ እንጂ» አሉትና «ሳያውቅ ሳያስብ ወይም ተደናግሮት በስህተት አላግባብ የከፈለው ገንዘብ ከሆነ መመለስ አለበት» አሉት።

አድማሱ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ቆመና እጁን ወደ ጋብቻው መዝጋቢ ሹም ዘርግቶ «እንግዲያውስ ሚስቱን ላገባ ለማዘጋጃ ቤቱ የከፈልኩትን ገንዘብ ይመልሱልኝ» አላቸው

ሹሙ ወደኋላቸው ለጠጥ አሉና በፈገግታ «ለምን?» ቢሉት «ሳላውቅ በስህተት ሳገባ የከፈልኩት ነው» አላቸው፤ ሹሙ ከት ብለው ሳቁ።

አድማሱ «ለምን ይስቁብኛል?» ብሎ ጠየቃቸው «ቀልደኛ ስለሆንክ ነው» አሉትና አድማሱ እየተናደደ ሔደ፤ አድማሱ ሐረገ ወይንን እንዳይፈታት ከሐረገ ወይን በኩል የሚቀርብለት መጥን አጓጓው።

እውነት አለው፤ በጎ በየሳምንቱ እየተሳበ የመጣል፤ ድልሁ በገንቦ ሽሮው ይጋዛል፤ አሻሮ አይቀርም፤ ጌሾው የሚመጣው እየተወቀጠ ነው፤ ሲሳይ ሞልቶል ዓለም ነው፤ ያ ባይሆንማ ኖሮ የአድማሱ ደሞዝ ከምኑ ጠብ ልትል?

እሱ ዘፍኖባት ለቤት ተሰጥታ ለውሀ መግዣ ሆና ከምን ልትበቃ? አድማሱም ይሔው ያውቃል፤ የሐረገ ወይን ወላጆች ቤት የተባረከ ቤት ነው፤ የአብርሃም ቤት ነው፤ ሚስቱ ደሞዙን አትጠይቀውም አንዳንዴ እሱው ሸቶ ገዝቶ ያመጣላት እንደሆነ እንጂ ገንዘቡን በየት አዋልከው አትለውም።

ይህን ጓደኞቹም ዘመዶቹም ያውቃሉ፤ ጠገብ እያለ ልፍታት ሲልም ገጪት የሚያደርጉት እነሱው ናቸው፤ ሐገረ ወይን ልጅዋን በወለደች በሦስት ወርዋ ያን ደም የሆነ ልጅዋን ይዞ ወደ ቤቶችዋ ዘንድ ሔደች።

አድማሱ የተገላገላት መስሎት ላገር ለሽማግሌ አስቸግሮ አልታረቃትም አለ፤ ቢሉት ቢያባብላት እምቢ አለ፤ ሐረገ ወይን ከቤቶችዋ ዘንድ ሔዳ በመቀመጥዋ አድማሱ ዓለሙን እንደ ልቡ ለመጥገብ ያራዳዎቹን ሲያማርጥ ከረመ።

አሥራ አምስት ቀን በማይሆን ጊዜ ውስጥ ኪሱ ተራቆተ፤ ቤቱም እኩል ተራገፈ፤ የሚቀመስ የሚላስ ጠፋ፤ ራት ምሳውንም ከወላጆቹ ዘንድ ይበላ ጀመር፤ የመንደሩ ሽማግሌዎች ሰብስቦ ወደ ሚስቱ አማላጅ ልላክ ቢል አማላጆቹ «በፊት እኛ እናስታርቃችሁ ብለን ብንይዛችሁ እምቢ ብለኸናልና አንሔድልህም» አሉት።

አጠፋሁ ማሩኝ በደልኩ ይቅር በሉኝ ብሎ አማላጆቹን ላከ፤ ሐረገ ወይን ደግሞ እምቢ በማለት አስቸገረች፤ ሽማግሌዎቹ ሁሉ ቆመው ራሱ አድማሱ እግርዋ ላይ ወድቆ ተለመነችና የምትፍራቸው አያትዋም ስለተቆጡ እሺ ብላ ታረቁ፤ ሲሳዩ እንደ ነበር ሆነ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አድማሱ ሐረገ ወይንን እንደ ጦር ይፈራት ያከብራት ጀመር፤ ያለ እሷ መቆም እንደማይችል የተገነዘበው ያኔ ነው። አድማሱ ሐረገ ወይንን ይፍራት እንጂ ጠባይ ሁና የተፈጠረችበትን የአመንዝራነት ባሕርዩን አልተው አለ።

የዚያን ጊዜ ሲታረቁ ዳግመኛ የአመንዝራነት ነገር ቢሰማት ፈጽመው ሊፋቱና ለመንግሥት የሺህ ብር መቀጫ ሊከፍል ገደብ ገብቶ ነው። ከዚያን ወዲህ አድማሱ ለጥ ሰጥ ብሎ መኖርን ጀመረ።

አንዳንድ አሳባቂዎች ወይም ደግሞ የነ አድማሱን ትዳር ለመበጥበጥ የፈለጉ ሰዎች ለሐረገ ወይን የአድማሱን የዕለት ሁኔታ ያቀርቡላት ጀመር፤ ሰዎቹ እውነታቸውን ነው፤ ያላደረገውን ያልሠራውን ዓይነግሯትም፤ ሐረገ ወይን እንዲህ እንዲህ ሥርተሃል ብላ የነገሯትን ስትጠይቀው «ሐሰት ነው፤ እንደኔ ጨዋ፤ የለም ግን እንደ ዕድል ብሎልኝ ሐሜት ይወደኛል፤ ዛሬ ልብ ገዝቻለሁ፤ ድሮ የልጅነት ጠባይ ይዞኝ ነው፤ ዛሬ ግን ሌላ ነገር አደርግ እንደሆነ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ እመኝኝ» ይላታል።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ አድማሱም ታማኝነቱን በመሐላ እየገለጸ ኖቱ፤ ሐረገ ወይንን ካላት ጠባይ ሁሉቀናተኛ ናት፤ አጥብቃ ትቀናለች፤ ስለዚህ ነው በቤታቸው የዘወትር ጭቅጭቅ የተፈጠረው።

ቅዳሜ ዕለት ካንድ ትልቅ ግብዛ ሁለቱም ተጠሩ፤ ሐረገ ወይን ልጅዋን አሞባት ነበርና መቅረቱን ሳትወደ ለልጅዋ ስትል ቀረች። አድማሱ ግን ከግብዣው ቦታ ሒደ። ሐረገ ወይን ልጅውና ስላመመው እያለቀሰ አቸግሯት ነበርና እንደምንም ስታባብለው አምሽታ በግድ በመከራ ተኛላት። እሷም እስከ ውድቅት ድረስ አድማሱን ስትጠብቀው ቆየችና ጋደም እንዳለች በዚያው አሸለባት።

አድማሱ ከግብዣ ቦት ሲጫወት አመሸና ወይም እንበለው አደረና ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ሲሆን ከቤቱ ገባ፤ ሐረገ ወይን ከመኝታዋ ተነሥታ ራትህን ብላ ብትለው ውስኪ የቦረቦረው አንጀቱ ጩርር እያለ ተይው ይብቃኝ አለ፤ ሐረገ ወይን ግን እንደራበው በሁኔታው አውቃ ገረዷን ጥርታ እራት እንዲቀርብለት አዘዘች።

አድማሱ ራቱን እስኪበላ ድረስ ሐረገ ወይን አጠገቡ ካለው ካንደኛው ወንበር ላይ ቁጭ ብላ «ታዲያስ ግብዣው ጥሩ ነበር ወይ?» አለችው።

«ኡ በጣም ጥሩ ነበር» አለ አድማሱ

«ዳንሱሳ ተሟሙቆ ነበር?» አለችው

«በጣም እንጂ እነ ሐሊማ የለሊቱ ኮከብ ሆነው ነበር» አላት

«ኦኬስትራው የማ ነበር?» አለችው

«አንቺ ኦኬስትራ ትያለሽ እረ ሌላ ጨዋታ ነበረ» አላትና የጎረሰውን ዋጠ።

«ምን ምን ጨዋታ ኖርዋል?» አለችው

«ብዙ ዓይነት ነበር፤ ግን ከሁሉም» ብሎ አላምጦት የነበረውን ዋጠና «ከሁሉም ያስደሰተኝ ሦስት ዳኞች ተመርጠው ወጡና ከፊታቸው አንድ ሙሉ ሻምፓኝ እንደታሸገ ተቀመጠ፤ በኋላ የ አክሊሉ ነበር ምሕረት በሚስቱ ላይ ማለት ሚስት እያለችው ከሌላ ጋር ያልባለገ ሰው እንዳለ ከመሐላችሁ ይወጣና ይህን ሻምፓኝ ይሸለም አለ፤ መቼም በዚያን ጊዜ የነበረው ሳቅ እንዲህ አይምሰልሽ» አላትና ጠቅልሎ አሰናድቆ ይዟት የነበረችውን ጉርሻ ጐረሰ።

ሐረገ ወይን ጠረጴዛውን ተደግፋ እንደተቀመጠች «ታዲያ ማን ተሸለመው ሻምፓኙን?» አለችው።

«ማንም አልተሸለመም» አላት።

«የወጣም ሰው የለ? ሚስቶቻቸውን እንኳ አፍረው የወጡ የሉም?» ብላ ሐረገ ወይን ጠየቀች

«እሱማ አሉ» አላት

«ታዲያ እንዴት አልተሸለሙም?» አለችው

«እባክሽ ያስቃል አላት፤

«እንዴት?» አለችው፤

«እንግዲህ ጨዋ ነም ይሉና ብቅ ሲሉ ከዚያው ከተጋባዡ መሐል የሚያቋቸው ይነሱና ጉዳቸውን ሲዘከዝኩባቸ ሰውየው ላይ የነበረው እፍረትና በሰው ላይ የሚታየው ሳቅ ለጉድ ነበር፤ መቼም እኔና ወንድምሽ ጌታቸው ልባችን ውልቅ ሲል አመሸ» አላት።

ሐረገ ወይን ወደ ኋላ ለጠጥ ብላ ወንበርዋን ተደገፈችና «ታዲያ አንተ ጨዋ ነኝ ትል የለም እንዴ? ለምን ለውድድሩ አልወጣህም ነበር?» አለችው።

አድማሱ ጠግቦ ነበርና የመጨረሻውን ጉርሻ ጎርሶ «በእርግጥ ለመሸለም እችል ነበር፤ እንኳን ሰው ሰይጣንም አይመሰክርብኝ፤ ግን አልወጣሁም» ብሎ እጁን ሊታጠብ ሔደ። ሐረገ ወይን አድማሱ የበላበትን ሳህን እያነሳሳች ጮክ አለችና «አንተ አታላይ ጨዋ ብትሆን ኖኦር አትወጣም ነበር?» ብትለው አድማሱ ከመታጠቢያ ሆኖ እየተጉመጠመጠ «ኖ ለሱ አይደለም» አላት «ታዲያስ?» ብትለው «ሻምፓኝ ስለማልወድ ስጦታውን ንቄው ነው» አላት።

አድማሱና ሐረገ ወይን በማነህ ማነህ ስድስት ዓመታ ያህል ኖሩ፤ ከመጀመሪያ ልጃቸው ከአረጋ ቀጥለው ወርቁንና አበባየሁን ወለዱ፤ የሦስት ልጆች አባት እናት ሆኑ።

ከጐረቤታቸው ያለችውን ሐመልማልን አድማሱ ወዳጅነት ይዟል እየተባለ በሰፊው ተወራ፤ ሐረገ ወይንም ይህንኑ ነገር ሰማታ ለመጣላትም ሆነ ለመቆጣቱ ደንበኛ ማስረጃ እስኪታገኝ ድረስ ትጠብቅ ጀመር።

ከሐመልማልም ጋር ሳትቀያየም እንደወትሮዋ ጓደኝነታቸውን አጸናች፤ በምንም ነገር ያልሰማች መስላ ታየች፤ ግን በልዩ ልዩ ዘዴ መረጃ የምታገኝበትን መንገድ ስትፈልግ ከረመች፤ ልፋትዋ ሁሉ ከንቱ ሆነ እንጂ የውጪው ሰው አድማሱ ሐመልማልን ይዞላ እያለ እንደሚያቦካው ሳይሆን ቀረ።

አንድ ቀን ነገሩን ፈራርጣ ጠየቀችው፤ አድማሱ ብዙ ተቆጣ፤ እንዴት እንደ እህቴ በማያት በሐመልማል ትጠርሪኛለች፤ ምንስ ብታስቢ አገኘሽው? እውነት አድርጌው እንደሆነ እግዚአብሔር ይፈርድብኝ ብሎ የተለመደ መሐላውን ማለ።

በማግሥቱ የአድማሱ ሦስት ልጆች ከነሐመልማል ቤት ሔደው ከሐመልማል ልጅ ከጥበቡ ጋር ከሳሎን ይጫወታሉ፤ ሐመልማል ከትልቁ ፎቴ ላይ ቁጭ ብላ ጥልፍ ትጠልፋለች፤ እነ አረጋና እነ ጥበቡ በሜዳው ላይ ፈስሰው በምድር ላይ ኳስ እያንከባለሉ ይጫወታሉ።

በድንገት ሳይትሰብ አድማሱ ዘው አለና ከመልማል ጋር ጨዋታ ጀመሩና «አንቺ? ሐረጓ እኮ ነገሩን ሰምታ ጠየቀችኝ» ቢላት ሐመልማል ደነገጠችና የምትጠልፈውን ጨርቅ ወርውራ «ወይ አፈር በሆንኩኝ» አለች።

አድማሱ የጀመረን ነገር ለማብረድ ብሎ «ኖ የለም ምዬ ስነግራት ጊዜ ዝም ብላለች» አላት፤ ሐመልማል መለሰችና «ምን ብለህ ነው የማልከውን?» ብትለው «ፈጽሞ አላደረኩም እንደ እህቴ ነው የማያት ብዬ ነው» ቢላት ሐመልማል ሳቅ አለችና «አፈር ብላ እቴ» አለችው።

ጥቂት ከተቀላለዱ በኋላ አድማሱ እስቲ ሳሚኝ ብሎ ጉንጩን ወደ ሐመልማል አስጠጋ፤ ሐመልማል እንደ ቀልድም እንደመቆጣትም ብላ «ወይድ ወዲያ» አለችና በጥፊ ለኮፍ አደረገችው። በዚህ ጊዜ አረጋ ጨዋታውንም ተወና ከቤት ውስጥ ወጣ።

ሐመልማል የአረጋን መውጣት ዓይታ ይናገራል ብላ ሰግታ ነበር፤ አድማሱ ግን «ልጁ የተቀጣ ነው፤ ነገር ግን ማወሳሰብ አያውቅም፤ ሲርበው እንኳን እንደ ልጅ ራበኝ አይልም፤ ደግሞ ምንም ነገር ቢያይ ያወራል ማለት ዘበት ነው እንዲህ አይምሰልሽ ጥሩ ጉጭማ ነው» አለና አበራረዳት።

አንድ አሥራ አምስት ቀናት ያህል ቆይታ የአረጋ ስድስተኛ የልደት በዓሉ የሚከበርበት ቀን ስለ ነበር የአረጋ ጓደኞችና ወላጆቻቸው ሌሎችም ሰዎች ሁሉ ለአረጋ የልደት በዓል መከበሪያ ዕለት ተጠርተው ነበር።

ሃያ ያህል እንግዶች ገብተው ሰላሣ ያህሎቹ ገና ሲጠበቁ ሐመልማል አንዲት በጣም ጥሩ በሆነ ወረቀት የተጠቀለለች ስጦታ ይዛ መጣችና ከበሩ ላይ ሁነው የተቀበሏትን አድማሱንና ሐረገ ወይንን ሰላም ካለች በኋላ እናትና አባቱ ሥር ተወሽቆ የተቀመጠውን አረጋን በርከክ አለችን ያመጣችለትን ስጦታ ሰጥታው «እስቲ ሳመኝ» ብትለው አራጋ ጉንጮቹን ነፋና «እምብዮ አባዬ ሊስምሽ ሲል በጥፊ እንደመታሺው እንድትመቺኝ ነው? » አላት።

# ሰውዬው።

ሰነፍ ነው፤ ሥራ ሲሉት ሳይሠራ ይደክማል፤ መብላትን እንኳ እንደ ሥራ ይቆጥረዋል። ብላ ከሚሉት ተጫወት ቢሉት ይወዳል። እየዞርክ ወሬ እይ ቢሉት ደስ ይለዋል። አጎቴም «ሰነፍ የሰነፍ መጨረሻ ነው» የሚሉት በዚሁ ነው። እንግዲያውማ የታላቅ ወንድማቸው ልጅ አልነበረም?

ዘር ከልጓም ይስባል የሚባለው ተረት በሰውየው ላይ አልዋለም፤ ሐሰት ነው። እውነትም ተረት ነው። እንግዲያውማ በምን አነሣኸኝ አይበሉኝና እንደሱ አባት ቆፍጣና፤ ታታሪ ሠራተኛ ነበር? የታወቁ ናቸው ስፌቱን የያዙት እንደሆነ፤ አንቱ የተባለ መሶብና መሶብ ወርቅ የሚሰፉ ናቸው። የዛሬን አያድርገውና የባላቸውን አርባ ክንድ

መቀነት የሚፈትሉ ነበሩ። በእርሻውስ ቢሆን! በጉልጓሎው፤ በአረሙ ማን ነበር ከእርሳቸው ወዲያ ሲተ?

ልጅ እንደ ወላጆቹ አይወጣም። አባ «የእሳት ልጁ አመድ» የሚሉት እውነታቸውን ነው። ቢወጣማ ኖሮ ቢያደርግለትም ኖሮ እኒያን ሰው ልጅ መች እንዲህ ይሆን ነበር? ሁን ያለው አይቀርምና ሆነ። አጎቱ «እንዲህ ዓይነት ሟላጣ በዘራችን የለ፤ እንዲያው በማን ይሆን የወጣው?» እያሉ የሚናገሩት መች ሐሰት ነው፤ ቤቱ የጀግና የጎበዝ ቤት ነው።

እንደ ምንም ተረድቶ ሥራ ይዟል። ሥራ መያዙ ሊሠራ ሳይሆን ለኑሮው መደገፊያ እንዲያገኝ ነው። ፊታውራሪ ናቸው የትም ወድቆ ይቀራል ብለው ደመወዝ የሚከፈልበትን ሥራ ለደመወዝ ያስያዙት።

መቀለድን፤ መሳቅን፤ ማሳቅን፤ መዞርን ይወዳል። በዚህ በኩል ችሎታ ያለው ይመረጥ ቢባል ማነው እሱን የሚቀድመው? ያውቃል፤ ያሳምራል፤ ማማት፤ መተቸት ሞያው ነው። አይሠራም እንጂ የተሠራውን ለመንቀፍ ማን ብሎት? ማንስ ቀድሞት?

ሞያው የሚታወቀው ከመጠጥ ቤት ወይም ከየሴቱ ቤት በየአምባው ነው። ሠራውሁ፤ ፈጠርሁ ያለኔ ምን ሰው አለ! ሲል የሚሰሙት ሁሉ፤ ሰማይን በጫንቃው ተሸክሞ ያቆመው ይመስላቸዋል። ትልቅ ነገር ተሠራ ሲሉ የሰማ እንደሆነ እኔም አለሁበት ይላል።

እሱ የማያውቀው ወይም ከመሥሪያ ቤቱ ጋር የማይነገናኝ መሠራቱን እያወሩ ሰዎች ሲያንደንቁ የሰማ እንደ ሆነ ማንኳሰስ ማበሻቀጥ ሞያው ነው።

በጠቅላላው ሰነፍ ብቻ አይደለእም። ምቀኛም ሳይኖ አይቀርም። ኮሎኔል ሲያወሩ «እኔ ብቻ ነኝ አዋቂ የሚልና ራሱን አኩርቶ ሌላውን የሚያንኳሰስ ሁሉ ተንኮልና ምቀኝነት አያጣምና አትጠጉት ይላሉ። እውነታቸውን ነው።

በየሰበቡ ፈቃድ ጠይቆ መውጣትን ይወዳል። ለወጉ ጧት ከሥራው ይገባል። አንድ ዶሴ ብጤ ይዞ ካንዱ ክፍል ወደ አንዱ ክፍል ላንድ አፍታ ይዘዋወርና ባንደኛው ቢሮ ሾልኮ ይጠፋል። ዓመሉ ይኸው ነው። ሁሉም አውቆበታል።

ከእሱ ጋር ያልተጣላ አለቃ የለም። እሱን ያልወቀሰ ያልመከረ አለቃና ሠራተኛ የለም። እሱን የሚወዱት የመሥሪያ ቤቱ ተላላኪዎች ብቻ ናቸው። ምክንያቱም ፈጽሞ ሰለማያዛቸው ነው። አለቆቹ ከሥራ እንዳያስወጡትም በገንዘብ እንዳይቀጡትም ያዝኑለታል። ብልት ብጤ በመሆኑ ለመላላክ ታዛዣቸው ነው። ተለማማጭ ነው። ድግስ የተደገሰ እንደ ሆነ ከእሱ እኩል አሳላፊ፤ አስተናባሪ ዘፋኝ ለዘበት ነው። ተፈልጐም አይገኝ፤ እሱው ነው ያለው።

አይብዛ እንጂ የደመወዝ ጭማሪም አያልፈውም፤ አለቆቹም ይኸንኑ የመላላኩና በየድግሳቸው መገኘቱ እንደ ውለታ እየቆጠሩለት ከሥራው እንዲወጣ በደመወዙ እንዲቀጣ አይፈርዱበትም።

ከሥራው የሚቀርበትን ፈቃድ ለመቀበል ምክንያት አያጣም፤ አባቱ ሞቱ ብሎ የሦስት ቀን ፈቃድ ወስዷል። ባልሞቱት በእናቱ አመካኝቶ ሦስት ቀን የኀዘን ፈቃድ ተቀብሏል፤ ያላገባትን ሚስቱን ሞታለች ብሎ አሁንም የሦስት ቀን ፈቃድ አግኝቷል። ያልወለደው ልጁ ሞተብኝ ብሎ የሦስት ቀን ፈቃድ ወስዷል። እነዚህ የሦስት ቀን ፈቃድ ያስገኙለት ናቸው። አንዴ አባቴ ሞተዋል ብሎ ፈቃድ ቢጠይቅ «ምነው ከዚህ ቀደም አባቴ ሞተዋል ብለህ አልተሰጠህም?» ቢሉት እንደ ገና ደግሞ በመጠየቁ ደንገጠና «የለም የክርስትና አባቴ ናቸው» ብሎ አጭበረብረ።

ከሥራው ለመቅረት እያለ ያልሞቱትን ዘመዶቹን ሁሉ ሞተዋል እያለ ጨርሷቸዋል። አለቆቹም እየታዘቡት «እንዲያ ያንተ ዘመዶች ሞተውም አያልቁ?» ሲሉት «ከትልቅ ወገን መወለድ ጣጣ ነው» ይላቸዋል፤

የሚወደው በደመወዝ ሰሞን ቀን ከሲኒማ ቤት፤ ማታ ከበረሃው መጨፈርን ነው። ኳስ ጨዋታማ ነፍሱ ነው። ከኪሱ ምንም ባይኖረው እንኳ በከተማው መዞርን እንጂ ከቢሮ መቀመጡ እንቅልፍ ያመጣበታል።

በደመወዝ ሰሞን ወደ ማታ ገደማ ያየው ሁሉ ወሩን ሙሉ ላንድ ቀን ደስታ ወደ በረሃ ወይም ወደ ቁራጭ ብቅ ያለ ከራኔ ይመስላል። ማጌጥ መድከም ነው። ተብሎለት ያለቀ ነው። አንዱም በአለቆቹ ዘንድ የሚያስወድደው ይኸው ንጽሕናውና መሽቀርቀሩ ነው።

ክራባትና ሸሚዝ ከማንም ጋ የለም። ቀስቶ ጫማው መሬትን የሚረግጥበት አይመስልም። በጠቅላላው ሸክ በማለቱ ሴቶችን ቀርቶ ወንዶችን የሚያስደነግጥ ቀልብ ያለው ልጅ ነው።

አንድ ቀን ከመሐል ከተማ አገኘሁትና «ታዲያስ እንዴት አለህ?» ብለው፤ «እባክህ ተቸግሬአለሁ» አለኝ።

«ምነው ምን ሆንክ?» አልኩት።

«ታምሜአለሁ» አለኝ።

«ምነው ምንህን ነው?» ብለው፤

«አሁንም የምሔደው መድኃኒት ልገዛ ነው» አለኝ።

«ምንህን ነው ያመመህ? አልኩት፤

«እባክህ ስተኛ ማቃዠትና ማኩረፍ ጀመረኝ» አለ

«ታዲያስ» አልኩት፤

«ተቸግሬአለሁ» አለኝ።

«ችግሩ ምንድነው?» ብለው፤

«ይኸን የሚያስኮርፈኝንና የሚያስቃዠኝን ነገር የሚያስጥለኝ መድኃኒት ማግኘት አለብኝ» አለኝ።

«ብታኮርፍስ ብትቃዥስ ምን ቸገረህ ባንተ አልተጀመረ» አልኩት።

«እሱስ በኔ አልተጀምረም» አለ።

«ታዲያ ምን ቸገረህ?» ብለው፤

«በየተቸገርኩበትማ ዋናው ምክንያት የቢሮዎቹ ሰዎች እባክህ አታደንቁረን እያሉ ስለሚቀሰቅሱኝ ነው» አለኝ።

እውነቱን ነው፤ ወንበሩ አልጋው ነው፤ ወንበሩ አልጋ የሚሆንለት ከሥራ ቦታ እንጂ ከሌላ ዘንድስ ወንበር ወንበሩ ነው እንጂ አልጋ አይሆንለትም። የሥራ ጓደኞቹም የእሱ ነገር በቅቷቸው ትተውታል። አምነው የሥራ አደራ አይጥሉበትም። ታዲያ ወዶ አይደለም። አንዴ ስንፍና ስለለመደና ባሕርዩ ስለ ሆነ ያን ልማዱን ለማስጣል አልተቻለም። እሱም አልሞከረም፤ ቢሞክርም አይሆንለትም።

ሐሙስ ዕለት ከአለቃው እንድ ቀረበና «አያቴ ስለ ሞቱ እንድቀብራቸው ፈቃድ ይሰጠኝ?» የሚል ማመልከቻውን አቀረበ። አለቃውም «አሁን እውነትህን ነው?» ቢሉት፤ «በእርግጥ እውነቴን ነው» አለና ማለቃቀስ ጀመረ።

«ቀብሩ ከየት ነው?» ቢሉት፤

«ከመድኃኔ ዓለም ነው» አላቸው።

«እንግዲህ እኛም ከቀብሩ እንመጣለንና በል ሂድ» ብለው ፈቀዱለት።

ፈቃድ የተቀበለው የዚያን ዕለት ባዘቦቱ የጊዮርጊስና የመቻል ቡድን ይጋጥሙ ስለ ነበረ ነው። የትም ሲዞር ዋለና ልክ ሰባት ሰዓት ሲሆን ከኳስ ሜዳ ከስታዲዮም ሔደ።

ከስታዲዮም ሆኖ ለሚደግፈው ቡድን እየረደ ሲጮህ ዋለ። ጨዋታው ከማለቁ በፊት ድምፁ በጩኸት ብዛት ተዘጋ። ድምፁ ስለሰለሰለበት የሚወደውን ቡድን የሚደግፍበት ድምፅ አጣ። ካጠገቡ ወደ ተቀመጠው ሰው ዞር አለና በዚያው

በለሰለሰው ድምፁ «ድምፄ ጠፋ» አለው። ዳኛው በጩኸቱ ሲቸገር ቆይቶ የነበረው «አልጠፋም! ሁሉም ከጆሮዬ ገብቶ አደንቁሮታል» አለው።

በነገታው ዓርብ ከመሥሪያ ቤቱ ገባ። አለቅዬው የሰውዬውን የክፍል ሹምና ፕርሶኔሉን ከቢሮአቸው አስጠርተው ከተሰበሰቡ በኋላ እሱ ተጠራና ገባ። እንደገባ «ትናንት የት ነበርክ?» አሉት አለቅዬው።

«እቀብር» አለ።

«መጥቼ አላጣሁህም?» አሉ።

«የለም ጌታዬ ሳለቅስ ነው የዋልኩት» አለ።

«ቀጣፊ ፈጽሞ አልነበርክም» አሉ አለቅዬው።

«ድምፄ እንኳ ይተዘጋው ከዚያው ሳለቅስ ነው» አለ

«ኳስ ሜዳ አልነበርክም?» አሉት አለቃው።

«አልነበርኩም» አለ።

«ከኔ በታች ተቀምጠህ ትጮህ አልነበረም?» ብለው አለቃው ቢቆጡት አፈረና ራሱን አካከከ። ወዲያው የፐርሶኔሉ ክፍል ሹም ሊደግፈው ፈልጎ፤ «ጌታዬ ዛሬ እንደሚያውቁት የስፖርት ፍቅር ተስፋፍቷልና አንፍረድበት ኳስ ጨዋታ ለማየት ብሎ ይሆናልና የሸዋው ይቅርታ ይደረግለት» አለ።

አለቅዬው እንደተናደዱ «እኔን እኮ ያናደደኝ አያቱን ሳይቀብር ኀዘኑን ትቶ ኳስ ሜዳ መሔዱ ነው» አሉ። የፐርሶኔሉም ሹም ወደ አለቅዬው ቀና ብሎ «በእርግጥ አያቱ ሞተዋል እንዴ?» ጠየቀ።

አለቅዬው ሲመልሱ «እኔ እሱን እሰልላለሁ ብዬ ከቤተ ክርስቲያን ብሔድ አንድ ሬሳ ታጅቦ ሲገባ ደረስኩና ብጠይቅ፤ የሞቱት የእሱ አያት መሆናቸን ነገሩኝ። ከለቀስተኛው መሐል ፈልጌ ስላጣሁት አንደኛውን ኀዘንተኛ ይህንኑ ጉድ ለምን ከቀብሩ እንደ ቀረ ብጠይቀው፤ ከባድ ሥራ ስላለብኝና በብርቱ ስለታዘዝሁ ቢሮ እሔዳለሁ ብሎን ሔደ። የመንግሥት ሥራ መቸም እናት አያስቀብርም አለኝ። በኋላ ወደ ኳስ ሜዳ ጨዋታውን ለማየት ብሔድ፤ ከዚያ ሲያናፋ አየሁት» ብለው ተናገሩና «አሁን መቀጣት አለበት» አሉ።

ይህስ ከሆነ ብለው ሁሉም ሊፈርዱበት ቃጡ። እሱ ግን «ጌታዬ ኳስ ሜዳ ሔደሃልና ተቀጣ ከተባልኩ እንደኔው የሔዱ ሁሉ ይቀጡ» ብሎ በገደምዳሜ ተናገረ። በዚህ ምክንያት ነገሩ ተድበሰበሰና ከአለቃው ቢሮ ወጣ። ከዚያ ቀን ጀምሮ ውልፍት እንዳይል አለቅዬው ወጥረው ያዙት።

ባይሠራም ከቢሮው እየገባ ሲያንቀላፋ ይውል ጀመር። ወሬ በማውራትም የሠራተኞቹን የሥራ ጊዜ ያጓትት ጀመር። ሐምሌ ሰባት ቀን ከአለቃው ቢሮ ገባና «የሁለት ወር ፈቃድ ይሰጠኝ» የሚል ማመልከቻውን አቀረበ።

አለቅዬው «ምን ያደርግልሃል የሁለት ወር ፈቃድ» አሉት።

«የዘንድሮው ክረምት በጣም ብዙ ብርድ ይኖረዋልና ክረምት እስኪወጣድ ወባ ስላለብኝ ይፈቀድልኝ ብዬ ነው» አለ ሲመልስ።

አለቅዬው የቀረበላቸውን ማመልከቻ አስቀመጡና ደንገጥ ብለው «ክረምቱ ብዙ ብርድ እንደሚኖረው ማን ነገረህ?» አሉት።

«ማንም አልነገረኝ» አላቸው።

«ከጋዜጣ ነው ያነበብኸው?» አሉት።

«የለም አላነበብኩም» አለ።

«በራዲዮ ተነገረ እንዴ?» ቢሉት፤

«የለም አልተነገረም» አለ።

«ታዲያ ብርድ እንደሚሆን በምን አወቅህ?» ቢሉ

«አውቀዋለሁ» አለ።

«እንዴት ነው የምታውቀው?»

«እቤት ያለቸውን ከሰል ሌባ ስለ ወሰደብኝ ነው» አላቸውና ተቆጥተው አባረሩት።

ፌዘኛ ነው፤ መቀለድን መቀባጠርን ይወዳል። ያንኑ ቅብጥርጥሩን እውነት አስመስሎ ማቅረብንና ማወናበድን አወናብዶ ማሸነፍን እንደ ጀብዱ ይቆጥረዋል።

መተኛት ይወዳል፤ ተኝቶ ለሀብት መመኘት ማአያው ነው፤ ሰማይ ተከፍቶ ከሰማይ የሚወርድ መልአክ የኔቱን ጣሪያ ቀዱ ብዙ ብር ካልጋው ላይ እንዲዘረፍለት ይመኛል። መልአኩ ይህን በሚያደርግለት እንኳ ሰብስቦ ከሣጥን መክተቱ የሚያደክመው ሥራ መሆኑ ይሰማዋል። ባጭሩ ገንፎ ከሰማይ ቢዘንብ ሰህን ይዞ አይቀበለውም።

እሱ ብቻ አይደለም፤ ገረዱም ያው ነች፤ አንድ ቀን ከቤቱ ጋደም ብሎ ጋዜጣ ሲያነብ በጋዜጣው ላይ የሎተሪ ዕድል የደረሳቸውን ሰዎች ታሪክ የሚዘረዝረውን ሲያነብ ገረዱ ሰማችና «ለኔም አንድ ቀን ሳይወጣልኝ አይቀርም» አለች።

«አንቺ የሎተሪ ትኬት ገዝተሽ አታውቂ፤ እንዴት ይወጣልሻል?» አይ ባኮቴ እግዜር ካለው አይቀርም» አለች፤ ከቤታቸው ነው፤ ከምስሶዋቸው ነው።

ማላገጡን አበዛው፤ አልመለስ አለ፤ ድሮ ያስቅለት የነበረው ቅልድ እያስከፋበት ሔደ፤ አትሚዘዝብን ይባል ጀመር፤ መለማመጡም የውሻ ሆነበት፤ በሁሉ ዘንድ እንደ አሮጌ ቁና ወይም በመንገድ ላይ እንደወደቀ አንደናቃፊ ጣሳ የሚገፋ ሆነ፤ አታደናቅፈን ባዩ በዛ።

የመሥሪያ ቤቱ ኮሚቴ ነበር ዶሴውን አገላብጦ አይቶ ለሥራ የማይጠቅም መሆኑን ስለፈረደበት ከሥራ እንዲወጣ ተወሰነ፤ በማግሥቱ እንዲለቅ በማግሥቱ እንዲለቅ የተጻፈለት ማዘዣ ደረሰው ጊዜ በጣም አዘነ፤ ከፉኛ ሲያዝንና ሲደነግጥ የመጀመሪያ ጊዜው ነው።

ራሱን በራሱ አታለለና ተፅናና «ሹፌርነት ተምሬ ሴይቼንቶ ብነዳም ይሆናል» አለ «ያለዚያም ካንዱ ፈረንጅ ሱቅ ተቀጥሬ ሸቀጣ ሸቀጥ ሻጭ ልሆንም እችላለሁ» አለ እነኝም ነገሮች የሚያደክሙት መሰለው።

«ግድ የለም ቀላል ሥራ ሞልቷል» አለ «አዝማሪነት ብቀጠርም ይሆናል፤ እሱም ደግሞ ዜማና ግጥም ማጥናቱ ልብ ያወልቃል» አለ «ደላላ ብሆን ይሻላል? አዎ ሳይሻል አይቀርም» ብሎ የደላላነት ሥራ ጀመረ። ከፒያሳ ይቆምና የሚደልለውን ነገር ሲፈልግ ይውል ጀመር፤ እሱ የሚያበስለው ፈላጊዎችን እንጂ ተፈላጊው የት እምኑጋ እንደሚገኝ አላጠናውም።

«ደህና የሚሸጥ ሸጉጥ ፈልገን» ይሉታል «ኡ እሱማ ከከዋጃ ሱቅ ሞልቷል፤ ከዚያ በርካሽ የፈለጉትን ዓይነት ሊገዙ ይችላሉ» ይልና የድካሜን ዋጋ ስጡኝ ይላል፤ «ሱቁንማ እኛስ መች አጣነው» ብለውት ያልፋሉ። እንኳን በቀን በሳምንት ቤሳም የሚያገኝ ደላላ ወጣው።

ተመረረ፤ ተበሳጨው፤ «ፈጣሪዬ እንዴት ፈጥረህ እንዳልፈጠርኸን ታረገኛለህ? አሁን ምን ቸገረህ እኔንም ከሰው እኩል ብታረገኝ?» ይላል እውነቱን ነው፤ ኑሮው ሁሉ ከሰው በታች ነው፤ ያለቸውንም ዕቃውን ቸብችቦ ጨርሷል፤ ልብሶቹም አለቁ፤ ደህና ደህናዎቹም የትርፍ ትርፍ ለማግኘት ከጨርቅ ተራ እየተንጠለጠሉ ይውሉ ጀመር።

አንድ ዘዴ አገኘ፤ «የተከበሩ ጌታዬ ሆይ፤ ያለ የሌለኝን ሀብቴን ሌባ ዘርፎኝ እንደሚያዩኝ ሆኘሎታለሁ ስለ ጭንቅ አማላጅዋ ስለ ተሰቀለው ጌታ ብለው የተቻሎትን ያህል እንዲመጸውቱኝ በወንድ ልጅ አምላክ ይገቼዎታለሁ» የሚል ደብዳቤ ጽፎ ይዞ ላላፊ ላግዳሚው ልስብ እያ ያስነብብ ጀመር፤ መጀመሪያ ለጥ ብሎ እጅ ይነሣል፤ እንዴት ዋልክ ሲሉት ወረቀቷን ይሰጣል፤ ያዘነ ሲሰጠው ሲሰጠው ሌላውም

ወይድ ባክህ እያለ ሲያልፍ ቢከፋውም ደስ ቢለውም «ጌታዬ ወረቀቷን ይመልሱልኝ» ማለትን ፈጽሞ አይረሳም።

አንድ ቀን ከድሮ ጓደኞቹ አንዱ አገኘውና አዘነለት፤ ጠቅላላ ሁኔታውንም ጠየቀው «እህል ከቀመስሁ ሦስት ቀኔ ነው» ስላለው ጓደኛው አዘነለትና ከሆቴል ቤት ወስዶ ምሳቸውን አብረው በሉ።

ከሆቴል ቤቱ ይበሉ የነበሩ ሁሉ ቆሻሻ በተንጨፈረረ ጠጉር፤ ኮት ያልደረበ በተቀዳደደ ሸሚዝ በክር በተጠቃቀመች ሸራ ጫማ ከፊትና ከኋላው በተቦጨቀ ቦላሌ ሱሪ አመድ መስሎ በገረጣ ቆዳ ያጌጠ ሰው በመሃላቸው በመገኘቱ ተጠየፉ ከዚያን ቀን ወዲህ እንኳን የሆቴል ቤቱ ደንበኞች ተቀነሱ።

ጓደኛው ምሳውን አበላውና ከበረንዳ ላይ አንዳንድ ቢራ ይዘው ሲጫወቱ ጓደኝዬው ድህነቱንና ያለበትን መከራ ሁሉ ከሰማ በኋላ እጅግ በጣም አዘነለት፤ በየወሩ እንኳ ሊረዳው ፈልጎ ነበር፤ ግን ለልጁ እናት ቀለብ ስለሚያሰፍርና በቤቱም ብዙ ወጪ ስላለበት ሊረዳው ባለመቻሉ አዘነ።

ጓደኛው ለጥቂት ጊዜ ተከዞ ቆየ፤ ወዲያውኑ ሰውዬው ከቢራው ጎንጩት አለና «ታውቃለህ? ዱሮ እንዲያ ያልተጫወትኩበትን ያህል አንድ ብር ለማግኘት እንደ ሰማይ ራቀኝ» አለው፤ ጓደኛውም ከተከዘበት መለስ ብሎ ለመቀለድ ያህል «አሁን እጅህን ከኪስህ ስትከት አሥር ብር ብታገኝ ምን ትላለህ?» ቢለው «የሌላ ሰው ልብስ አሳስቼ ለብሼ ነው እላለሁ» ብሎ መለሰለት፤ ከዚህ በኋላ ለእራቱ ሙብያ ሃምሳ ሣንቲም ከእጁ ላይ አደረገለትና ተለያዩ።

አንድ ቀን የድሮ ጓደኞቹ ከሥራ ወጥተው በወደማታው አየር እየተናፈሱ በፒያሳ ሲያልፉ ሰውዬው ማስታወቂያ እየተለጠፈበት አንዳንድ ልጆች እየተሸከሙ የሚያዞሩትን ካርቶን ከጀርባና ከፊቱ በጠፍር አንጠልጥሎ ሲዞር አገኙት። በካርቶኑ ላይ የተጻፈበት ወይም የተለጠፈበት ማስታወቂያ አልነበረም፤ ፍጹም ነፃ የሆነ ባዶ ካርቶን ነበር።

ጓደኞቹ ለጥቂት ጊዜ ቆም ብለው አዩትና «ምነው ባዶ የማስታወቂያ ማዞሪያ ካሮትን ተሸክመህ ትዞራለህ? ይህንንስ እንድታዞር ማነው በዋጋ የተዋዋለህ ሞኝ» ቢሉት «ሞኝ ተግኝቶ የሚዋዋለኝ አላገኘሁም« አላቸው «እንግዲያውስ እንዴት ነው? ቢሉት «ሥራን ልልመድ ብዬ ነው» አላቸው።

# ሙቶ ሽህ ብር?

አቶ ዡማነህ ከማህል አራዳ አገኙኝና «ብርቱ ጉዳይ ስላለኝ እቤቴ ድረስ እንድትመጣ፤ በብርቱ ነው የምፈልግህ» ስላሉኝ ረቡዕ ዕለት ከሥራ እንደወጣሁ በቀጥታ ካቶ ዡማነህ ቤት ሔድሁ።

ምሳ በልተን ቡና ስንጠጣ የተፈትለግሁበትን ጉዳይ ያወሩልኝ ጀመር፤ ለልጃቸው ለሣራ ባል መምጣቱን ነገሩኝ፤ የመጣውንም ባል አውቀው እንደ ሆን ጠየቁኝ እንደማላአውቀው ነገርኳቸው፤ ሁኔታውን እንዳጣራላቸው ለምነውኝ ተለያየን።

አውቃለሁ፤ አቶ ጀማነህ አንዲት ቅንታት ልጃቸውን ለማንም የአራዳ ወጣት የሚሰጡ አይደሉም፤ ብዙዎች ናቸው ሣራን ለማግባት እየጠየቁ ሳይሳካላቸው እየቀረ የተው፤ አጥንት ያስፈልጋል፤ የማነህ ሲሉት የእከሌ ነኝ በማለቱ ብቻ እንዲታወቅ ያስፈልጋል የእከሌ ነኝ ብሎ እከሌ የማነው እንዲባል አያስፈልግም።

«ጋብቻዬ የሚሆነውን ባቋቋሙ ነው የማውቀው» ይላሉ፤ ደፍሮ የሚጠይቅ የለም እንጂ ከጠየቀ ሣራን ለማግባት የሚቀርብለትን ፈተና ሁሉ ማለፍ ይኖርበታል፤ ኋላማ እንደ ሣራ ማማር ፳፯ ዓመታት ሙሉ ሙች ባል ሳታገባ ትኖር ነበር?።

የሰው ልጅ በእውቀቱ እንጂ በትውልድ አያድግም የሚለውን ዘመን አመጣሹን የንግግር አቃቂር አቶ ዡማነህ አያምኑበትም፤ እምነታቸው በዘራቸው የታወቁ ሰዎች በታወቀ ቦታ መዋል አለባቸው ነው።

በዚህ ምክንያት ነው ሣራ ባል ሳታገባ ሐያ ስድስት ዓመታት ሙሉ ከእናት ካባትዋ ጉያ የኖረችው አባዋ የዋዛ ሰው አይደሉም፤ ለልጃቸው ለሣራ የሚመጣለት እጮኛ በዘሩ‐ታላቅ እንዲሆንና ሀብቱም አንፍጫው አጠገብ ባይደርስ እንኳ አገጩ ገደማ የደረሰ እንደሆን ይፈልጋሉ፤ ስለዚህ ነው ያቺን የመሰለች ቀዘባ ባል ሞቶ ተትረፍርፎ አጥታ የኖረችው።

ካቶ ዡማነህ በተላየየን በስምንተኛው ቀን ተገናኘንና «ታዲያስ ያልኩህን እንዴት አደረክ?» አለኝ «አጣሁት» አልኳቸው፤ «ማወቅማ እኔማ አላወቀውም ሁሉንም ነገር የነገረችኝ ሣራ ነች እኔም እሺ እጣራለሁ ነው እንጂ ያልኳት ሌላ አላልኳትም እስቲ ለሁሉም እሱዋን እንጠይቃት» አሉና በአውቶሞቢላቸው ወደ ቤታቸው ሔድን።

ምሳ ከበላን በኋላ ከእልፍኝ ሆነን ስናወራ አቶ ዡማነህ በተለያየን በስምንተኛው ቀን ተገናኘንና «ታዲያስ ያልኩህ እንዴት አደርክ?» አሉኝ «አጣሁት» አልኳቸው «ማወቅማ እኔማ አላወቀውም ሁሉንም ነገር የነገረች ሣራ ነች እኔም እሺ አጣራለሁ

ነው እንጂ ያልኳት ሌላ አላልኳትም እስቲ ለሁሉም እሱዋን እንጠይቃት» አሉና በአውቶሞቢላቸው ወደ ቤታቸው ሔድን።

ምሳ ከበላን በኋላ ከእልፍኝ ሆነን ስናወራ አቶ ዠማነህ ለጠጥ ብለው ተቀመጡና ሣራን «እስቲከ የዚያን ሰው ሁኔታ አጫውቺኝ» አሏት።

«ምን መሳይ ነው?» ብላት ጣቶችዋን ጋር አቆላልፋ ዓይኔን እያየች «ጠይም ነው» አለችኝና ፈገግ አለች።

«የማን ልጅ ነው? አባቱ የታወቁ ናቸው እንዴ?» አልኳት፤ ሣራ መልስ ልትሰጠኝ ስትሰናዳ እናቷ ወይዘሮ ሙላቷ በመሐላችን ጣልቃ ገቡና «ዛሬ እኮ ዘር ቀርቷል፤» ብለው ሳጨርሱ አቶ ዠማነህ አቋረጧቸውና «ይቺ ሴት ጤናማ አይደለች? ይሔን ጥልቅ ማለት ተይ አላልኩሽም? አንቺ አሁን ስለ አደባባዩ ሁኔታ ምም ታውቂና ነው?» ቢሏቸው ወይዘሮ ሙላቷ እንደማኩረፍ ብለው «እኔ ምንቸገረኝ እንደፈቃዳችሁ፤ በኋላ ዲቃላ ማሳደጉ ብቻ እንዳይቸግረን» እያሉ ወደ አንደኛው ክፍል ገቡ።

«ልጁ እንኳን» ሲሉ አቶ ዠማነህ ጀመሩ፤ «ልጁ እንኳን በዘሩ ምንም አይል፤ ባሻ መሽሻም አጫውቶኛል፤ ጠባዩም ደህና ነው አሉ፤ ቢሆንም ማን እንደራስ ይሆናልና አንተ ብታጣራው ይበጃል በመቶ ሺህ ብር የሚገመት ሀብት አለው ይላሉ፤ ከሰው የሰየሙትን ይዘው ነው እንዴት የመቶ ሺህ ብር ሀብት ሊኖረው ይችላል ብዬ ነው፤ ወርሶ እንደሁ አላውቅም፤ ከወረሰም ማለፊያ ነው፤ ቢወርስም ልጅ ነውና እንዴት መቶ ሺህ ብር ሊያኖር አለ እላለሁ፤ ከቻለ በውነት ጨዋ የዛሬ ልጅ ይሄን ያህል ሀብት ካጠራቀመ ወይም ያገኘውን ካስቀመጠ በውነቱ ክፍል የተገኘ ጥሬ ነው ልንለው ይገባል ሳላወላውልም ልጄን እድርለታለሁ፤ ብቻ ለሁሉም ነገር እኔ አልመሰለኝምና ይሔ የሰው ሀይሀይታ ስለማያዋጣኝ አንተ አጥራልኝ» አሉኝ።

በዝምታ ካዳመጥኳቸው በኋላ ወደ ሣራ ዞር ብዬ «ታዲያ እንዴት ነው እናንተ የተነጋገራችሁት?» ብዬ ጠየቅኋት ውሽቷን ሳቅ አለችና ተቅለሰለሰች፤ አባትዋን አፍራ ነው፤ አስትውቆባታል እየተሽኮረመመች አቀርቅራ አባትዋን ታይ ነበር። እሳቸውም በመሆኑ ገብቷቸዋል፤ «እስቲ እናንተ ተጫወቱ፤ እኔ የቀን እንቅልፍ ተቸግሬአለሁ፤ እንግዲህ አይምሰልህ ከበደ፤ ተቸግሬልሃለሁ» አሉና አቶ ዠማነህ ወደ መኝታ ቤታቸው ሔዱ።

«አየህ ጋሽ ከበድዬ» አለኝ ሣራ «ልጁ ደህና ልጅ ነው መረተም በቀደም ሁሉንም ነግራኛለች ሐመረእንኳ ደህና የተማረ ልጅ ነው ብላኛለች፤ ደሞም ታጋሽ ነው፤ ነገሩን ከጀመርነው ዓመት አልፎአል ግን እኔኑ ይጠብቃል፤ እሺ ሌላ ሰው ቢሆን ይህን ያረጋል? አያረግም ውሸት ምን ያረጋል።

«አየህ ብቻ በቂ የቃል ንግግር አላደረግንም እንጂ ብዙ ደብዳቤዎች ተጻጽፈናል የኛን ቤት እንደምታውቀው ከሱ ጋር ሳወራ ያዩኝ እንደሆነ ቁም ሥቃዬን ነው የሚያሳዩኝ እናትዬ።

«እሱም ይህንኑ አውቆ ተጠግቶ ሊያወራኝ አይፈልግም፤ ይሔም ራሱ አንድ ጭዋነት ነው፤ ማለቴ እንደ ሌሎቹ ደፋር ባለመሆኑ ነው፤ ታውቃቸዋለህ የዛሬዎቹ መገለጢጦች እንዴት እንደሚሆኑ በመንገድ እንኳ አላሳልፍ አይደል እንዴ የሚሉት» አለችኝ።

ጉልበቶቼን ተመርኩዤ ፈዘዝ እንዳልኩ «ደመወዙስ?» ብዬ ሳልጨርስ ሣራ አቋረጠችኝና «በቂያችን ነው፤ አየህ የዘመኑኑን ነገር እንደምታውቀው በወገን ሆኖ ጨቄውት ነው እንጂ በሥራው የተወደደና የተመሰገነ ነው፤ እሱም ጐበዝ ነው፤ እንደሰማሁትና እንደሰማኸው መቶ ሺህ ብር የሚያወጣ ሀብት አለው፤ አሁን ደሞዙ ፫፻፶ ብር ነው፤ ታዲያስ በቂ ነው።

«የቤት ኪራይ የለበት፤ እህል አይገዛ፤ ደሞዙ የሚስ ገንዘብ መሆኑ ነው፤ ጥሩ ቪላ ነው አሉ ያለ ከደመወዙ ሌላ የመቶ ሺህ ብር ሀብት እንዳለው ነግረውኛል፤ ይሔ ደሞ እውነት ነው፤ እትዬ ልኬለሽም ይህንኑ አጣርታ ነግራኛለች፤ ላባባም ነግራዋለች፤

«እንግዲህ እሺ እሱ ቢዋሽ እትዬ ልኬለሽ ትዋሻለች? ለማን ብላ ነው የምትዋሸው? ማን ሊቀርባት? እሱ ሲቀር የሚቀር ባዕድ ነው፤ እኔ አይደለሁም እህቷ እንዴ? ከደህና ሰው ነው ያጣራሁት ብላለች።

«በውነቱ ጋሽ ከበድዬ የጻፈልኝልን ደብዳቤ ባሳይህ ታዝናለህ፤ ማለቴ እንዲያው ምን ልበልህ አንድ ፍርድ ትወስደብታለህ፤ አሁን እንዳላሳይህ መኝታ ቤት ነው፤ አባዬ ተኙ እንጂ አሳይህ ነበር፤ ምን ልበልህ ተራቆ ነው የጻፈልኝ ደሞዝ የቃል አወጣጥና አሰካክ እማንጋ አለ ልሙትልህ ጋሽ ከበድዬ እንደ ሌሎቹ አበድኩ ሞትኩ ከነፍኩ አላለም እቅጯን ነው የተናገረው፤ ያ ጋሽ ጥበቡ ያመጣው ዛላውን አሳምሮ እንዲህ ብሎ አልቀረም? የጻፈልኝን አንብበኸዋል፤ ምየልህ ጋሽ ከበድዬ እነኝህ ሞትኩ ከነፍኩ የሚሉ ሁሉ ውሸታሞች ናቸው፤ ላያገቡ ነው አገባሻለሁ የሚሉት ተዋወቅን» አለችኝ።

«ታዲያ አሁን እንዴት ነው? ብላት «አባባ ይሔ ሰውዬ መናጢ ነው እያሉልህ እንቢ አሉ፤ ውቃቢዬ ነግሮኛል ይሉልሃል፤ ወፋብኮ አይደሉ፤ ሁሉም ቢነግሯቸው አላምንም ብለዋል፤ ቆይ ታያለህ አንተም አሁን እውነቱን ስትነግራቸው ኤድልኝ አትረባም ነው የሚሉህ።

«እሺ ጋሽ ወልደ ሰማዕትን ያህል ሰው ለሳቸው ብሎ እሳቸውን ፈርቶ ነገሩን አጣርቶ ሁሉም ነገር እውነት መሆኑን ቢነግራቸው የለም አላጣራኸውም አሉትና ቁጭ፤

«ጋሼ ወልደ ሰማዕትን ነገር ታውቀዋለህ፤ ለራሱ ቁጡ ነው፤ አይ እንግዲህ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ያጣራሎት አላቸውና ውልቅ አለ፤ ባል አልተፋ፤ አንቺ ምረጭ ይሉኛል፤ ስመርጥ ደግሞ የማያውቁትን አይረባም መናጢ ነው ይሉልሃል፤ እንዲያው እንዴት መሰለህ።

«አየህ፤ ደሞ ሰው ዕድሜዬን እየቆጠረ ቆማ ቀረች ይለኛል» ስትል አቋረጥኳትና «እሱን እንኳን ተይው፤ ቢሉሽ ምንቸገረሽ» አልኳት፤ ሣራ አዘን አለችና «እሱስ ግድ የለኝም፤ ብቻ አየህ ወይኒቱን አሁን የስንት ጊዜ ታናሼ ነች፤ ሁለት ወልዳ የለ» አለች።

«ይሔን አትበይ» ብላት

«ሰው እኮ ይሔን ነው የሚያመዛዝንልህ» አለች፤

«የሰውን ነገር ተይው፤ አሁን የወይኒቱ ባል መሆኑ ነው?» አልኳት

«እሱስ እወንትህን ነው» አለችኝ፤

«ይሔ ለራሱ ሰካራም፤ እንዴት አደርክ ሲሉ ደህና አምሹ የሚል ባል ነው? ያኔ አጎትሽ አኩለው ነው የዳርዋት፤ መቼም ወልዳለችና ምን እናድርግ ብሎ ነው ዘመድ ሁሉ ዝም ያለው፤ መጣራተጉ እንኳ አይከፋም» አልኳት።

«መች ክፉ ነው አልኩ፤ ግን ጋሻ ወልደሰማዕት፤ እትዬ አስካለ፤ አበባ ይፍሩ፤ እትዬ ልኬለሽ እነኝህ ሁሉ ሰልለው አጣርተው ነገሩዋቸው፤ እሳቸው ብቻ የለም ልክ አደላችሁም ይሏቸዋል፤ ስድስተኛ ነህ ሰባተኛ ነው አሁን አንተን አጣራ የሚሉት» ስትለኝ አቶ ዡማነህ ከመኝታ ክፍላቸው መጡ።

አቶ ዡማነህም ከእልፍኙ መውጫ በር ላይ እንደ ቆሙ ካፖርታቸውን እያስተካከሉና እየነቃቀሉ ከኋላቸው ለቆምኩት «እንግዲህ ሁሉንም ነገር አንተ አጣራው፤ ጮሌ ነህና እንደማይመልጥህ አውቃለሁ፤ ይሔን የዘመኑን ልጆች አነጋገር እምብዛም እምነት አልትልበትምና አንተ አጣራልኝ፤ አማላጆቹንም በዚሁ አቆይቻቸዋለሁ» ሲሉ በነገራቸው መሐል ጣልቃ ገባሁና «አማላጆቹ ስለ ጠባዩ ምን አሉ?» ብላቸው «ጠባዩ ጥሩ ነው ብለውኛል፤ ስለ ሌላው ነገር ግን ምንም አልጠየኳቸውም፤ እንደሰማሁት ሰውዬም ቢሆን ለጋብቻው የሚቸኩል አይመስለኝምና ጊዜ አለህ» አሉኝና አብረን ሔድን።

ትልቅ አደራ ነው፤ አቶ ዡማነህ ቢቀየሙ የሚጎዱ ናቸው፤ በእሳቸው ዘንድ ልክስክስ ሆኖ መገመቱ ከንድፍ ይልቅ የቀለሉ ሆኖ መገኘት ነው ልጅ ሽብሩ አንድ እቅን በቀላመደ ነው እስከ ዛሬ ጠምደው የያዙት፤ በዚሁ ነው ለየሰው ሁሉ የማያድግ ነው እያሉ የሚያወሩት፤ ማጣራት አለብኝ በእርግጥ ጥሩ አድርጌ ማጣራት አለብኝ፤ መጀመሪያ የነገሩን ፍንጭ ለማግኘት ያህል ከወየሮ ልኬለሽ ዘንድ ሔድሁ፤

እግዚአብሔር ያከብራቸውና ያን ሁሉ ሥጋቸወን እንደ ተሸከሙ እበር ድረስ ወጥተው ተቀበሉኝ፤ ዋ አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ ሆነ እንጂ ወይዘሮ ልኬለሽ እኮ ትናንት እርም ታህል የነበሩ ልጅ ነበሩ፤ ምናላቸው ይባልላቸዋል፤ እርግጥ ነው ቆዳቸው ይመሰክራል፤ የውፍረት ይሁን የበሽታ እንጃ እንጂ ከጊዜ በኋላ ነው አሉ እግራቸው የተድበለበለው።

ስለ ሣራ እጮኛ ብጠይቃቸው እርግጥ ልጁ ብዙ ሀብት ያለው መሆኑንና የጨዋ ዘር መሆኑንም ነገሩኝ።

«እንዴት ይህን ለማወቅ ቻሉ?» ብላቸው፤

«ለገሡን አጣራ ብዬው ነበር፤ ነገሩን መርምሮ እንዳገኘው ልጁ ምራቁን የዋጠ ጨዋ ነው ብሎኛል» አሉ።

«ይሔስ የመቶ ሺህ ብር ያህል ሀብት አለው የሚባለውስ» ብላቸው

«እርግጥ ነው አሉ፤ አለው አሉ» አሉኝ።

ሌላ አልጠየኳቸውም፤ የተሰጠችኝን ውስኪ ጨልጪ ወጣሁ፤ ወይዘሮ ልኬለሽ እንኳን እንዳጫውታቸው ፈልገው ነበር፤ እግረ መንገዳቸውንም ስለ ሚስቴ ጉዳይ አንስተውብኝ ነበር፤ እኔ ግን ቸኩዬ ነበርና ነገሩን ቸል ብዬው ሔድሁ።

አቶ ወልድ ሰማዕትም ዘንድ ሔድሁ፤ እሳችወም እንደ ወይዘሮ ልኬለሽ ነገሩኝ፤ የወሬ አባታቸውም ያው ለገሰ መሆኑን ነገሩኝ፤ ወይዘሮ ምንትዋብ ዘንድ ሔድሁ፤ እሳቸውም ልክ እንደ አቶ ወልደ ሰማዕት ነገሩኝ፤ ወሬውንም ያጣርላቸው ሾፌራቸው እጅጉ መሆኑን አጫወቱኝ፤ ወይዘሮ አስካለ ዘንድ ሔድሁ፤ እሳችወም ልክ እንደ ወይዘሮ ምንትዋብ ነገሩኝ፤ የወሬ አባታቸው የወይዘሮ ምንትዋብ ሾፌር እጅግ ነው አሉኝ።

ከዚህ የበለጠ ምስክርነት አያፈልግም፤ አቶ ወልደ ሰማዕትም ቢሆኑ ጠጉራቸውን ሽበት የወረረው በራ በመሆናቸው የሚታመኑ አረጋዊ ናቸው፤ ሁሉም የማይዋሹ ቤተሰቦች ናቸው፤ ከዚህ ወዲያ ነገር አያብዙ ብዬ አቶ ዝማነህን ልቆጣ ወደ ቢሮአቸው ሒህድሁ ግን ሳያቸው ሳይቆጡኝ ደነገጥሁ፤ የአስደንግጥ አዚም አለባቸው።

ነገርኳቸው፤ «ከነሱ ወዲያ ምስክር መፈለግ አፍን ማበላሸት ነው» አልኳቸው። «እባክህ ተውኝ» አሉኝ «ሰንፈህ እንደሆን ንገረኝ እንጂ እኔ እነሱን አላመንኳቸውም፤ የት ተዟዙረው ስገናኙ ነው? የሰ ወሬ የዘው ነው የሚከተፍሱት» አሉኝ።

«ታዲያ አንተው አጣራ ነው የሚሉኝ?» ብላቸው «አዎ አንተ ሁልገብ ስለሆንክ ነገር አያመልጥህም፤ እውነቷን ልታገኝ የምትችለው አንተ ነህ» አሉኝ።

«እኔም ልክ እነሱ እንዳሉት ሆኖ ባገኘውስ?» ብላቸው፤

«እደርስበታለሁ» አሉኝና «አንተ ቦርቡረህ ውስጡን አውቀህ ልክ መሆኑን ከነገርከኝ እድራታለሁ፤ ግን ተጠንቀቅ» አሉኝ፤ እሺ ብዬ ተሰነባብተን ተለያየን።

አሰበሁ፤ በእንዴት ዓይነት ዘዴ ለማጣራት እንደምችል አሰላሰልሁ፤ ያልወጠንኩት ያላሰላሰልኩት ሐሳብ የለም ከሁሉም የተሻለ ሆኖ ያገኘሁት ከሰውዬው ጋር ጓድ መሆንን ነው።

አንዱ ችግር ደግሞ ከሰውዬው ጋር መተዋወቁ ነው፤ ሣራ ሰውዬው ጋዜጠኛ መሆኑን ነግራኝ ነበር፤ በሚኒስቴሩ ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ጋዜጠኞች የሱ መሳይ ስም እንደ ሌላቸው ተረዳሁ በየጋዜጦቹ ላይ አንዳንድ ድርሰቶችን ስለሚጽፍ ይመስለኛል ሣራ ጋዜጠኛ ነው ያለችኝ።

ሣራ ከተማሪ ቤት ስትመለስ ከመንገድ ላይ ተገናኝተው ሲነጋገሩ በሩቁ እየጓቸውና ሰዬን አወቅሁት፤ ሣራም እሱው መሆኑን ነገረችኝ፤ አሁንም ችግሩ ከሰውዬው ጋር መተዋወቁ ነው።

የሀገር ቤት ሰዎች አይደለንም፤ ወይንም ያንዲት መጠነኛ መንደር ነዋሪዎች አይደለንም፤ ሁለታችንም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ነን፤ ባሕር ነው፤ ውቅያኖሳችን ነው፤ የቅርብ ጎረቤቶች እንኳ የማይተዋወቁበት ከተማ ነው፤ ሁሉም ተኳርፎ የሚተላለፍበት ነው፤ እንዲያው ደርሶ ከመንገስ እንዴት ዋልክ ቢሉት የት ታውቀኛለህ? ተብሎ የሚጠየቅበት ነው፤ ባጭሩ አዳሜ በሙሉ የሚተረማመስበት ከተማ ነው።

እዚህ መሐል እዚህ ሁሉ ግርግር መሐል ባሕር ላይ እንደ ወደቁ ሁለት የዝናብ ጠብታዎች የሆነው እኔና ሰዬው የት ተገናኝተን እንዴትስ እንተዋወቃለን? እንዴትስ ባጭር ጊዜ ውስጥ አፍ ያልን ሚስጢር ተካፋይ ጓደኞች እንሆናለን? ለየትኛው ታቦት ቢሳሉ ነው የልቤን ዘከዝኬለት የልቡን የሚዘከዝክልኝ? ጭንቅ ነው፤ አይተውት ነገር ያቶ ዠማነህ ትእዛዝ ነው።

መሥሪያ ቤቱን አወቅሁት፤ ሁልጊዜ ማታ ማታ ከሥራው ሲወጣ እከተለዋለሁ፤ ግን ልጁ አንገተ ሰባራ ጨዋ የጨዋ መጨረሻ በመሆኑ በቀጥታ ከቤቱ ይገባል፤ የትም ውልፍት አይልም፤ ይሔም አስቸገረኝ፤ ከማያውቁት ቤት፤ ቡና ከተጋበዙበት ቤት ወይም መጠጥ ከማይሸጥበት ቤት እንዴት እንዲያው ዘው ይባላል?

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ከሥራው ወጥቶ ሲሔድ እንደ ተለመደው ተከተልኩት፤ ፒያዛ ደረስን፤ ከጓደኛው ጋር ከቼንትሮ ቡና ቤት በራፍ ላይ ተቀመጡ፤ ባንደኛ አገጠባቸው ካለው ጠረጴዛ እኔ ተቀመጥሁ፤ እኔም እንደነሱው ቡና አዘዝሁ።

አሁንም አንድ አስቸጋሪ ነገር ነበር፤ ከማያውቁት ሰው ጋር እንዲያው ዘው ብሎ ጭውውትን መክፈት አስቸጋሪ ነው፤ ሰካራም ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል፤ ያም ቢሆን ጥፊ ይከተላል።

የምፈልገው ጥቂት ሰበብ ነው፤ የዝንብ ማንኮሻኮሽ ሊስትሮዎች፤ ሱቅ በደረቴዎች ሁሉ ሰበብ ሊሆኑኝ ይችላሉ፤ አዎ ሆኑኝ።

«ረፍት ፈልጎ ከዚህ ያረፈ ሰው አልገዛም አላስጠርግም በማለት ልቡ ሊወልቅ ነው፤ ከቅድም እስካሁን ለስንቱ መልስ ሰጠን» ብዬ ፈገግ አልኩና ከበስተግራ ከበራፍዋ አጠገብ ለተቀመጡት ነገርኳቸው።

«አዎ በጣም ችግር ነው» አለኝ ሰውዬው «ምነው ማዘጋጃ ቤት አንድ መፍትሔ ቢያደርግ?» አለና ሁሉም እንደ ልቡ ሳይፈራ የሚያማውን ማዘጋጃ ቤትን አማልኝ፤ ወሬው እንዳይቋረጥም ገፋገፋ አደርገው ጀመር፤ በዚያው እያራዘምን እግረ መንገዳችንን ወሬውን እያበዛን ሔድን።

በኋላም እየቆየን ተላመድንና ባንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጥን፤ ቶሎ በቶሎ እንድንግባባ በማለትም ገፋ ገፋ እያደረግሁ ጋበዝኳቸው፤ ከቡና ቤቱ ገባን፤ ከዚያም ቢራችንን እየቀዳን ወሬአችንን እንቀዳ ጀመርን።

እኔም ብሆን ለጓደኝነት የምፈልገው ወጣት ነኝ፤ አለባበሴ ከማንም ሊያቃርበኝ የሚችል ነኝ፤ እንዳያስገምተኝ አነጋገሬን አስቤ የምጥል ነኝ፤ አረማመዴም ቢሆን በሕግና በወግ በመሆኑ ማንም ለጓደኝነት የሚመርጠኝ ነኝ፤ እንኔ ከቤ ራሴን የማውቅ ራስ ያለኝ ነኝ፤ እነሱም ቢሆኑ ተደስተው ቶሎ ያስጠጉኝ በዚሁ ነው። ስሜ ከበደ መሆኑን ነግሬው ስሙ እሸቴ መሆኑን ነግሮኛል።

ከዚያን ዕለት ጀምሮ አዘውትረን የምንገናኝ ጓደኛሞች ሆን፤ ለሦስት አራት ቀናት ያህል ከቤቴ እየወሰድኩት ጋበዝኩት፤ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ከቤቱ ወሰደኝ፤ ቤት ያፈራውን ጋበዘኝ።

ቤቱ እጥር ምጥን ያለች ትሁን እንጂ የዕቃዎቹ አቀማመትና ንፅሕና አበበ ጎጆውን አሸንፎ የሞኖር ሰው መሆኑን ይመሰክሩለታል፤ ገረዱ ተዋበች አልስማማ ብላው ማባረሩና በሆቴል ተመጋቢ መሆኑን ነገረኝ።

«ለምን ሚስት አታገባም?» አልኩት፤

«አገባለሁ» አለኝ።

«አጭተሃል ወይ?» ብለው ራሱን አካከከና ቅር እያለው «አዎ አጭቻለሁ» አለኝ።

«ምነው ቅር አለህ?» ብለው

«ከልጅቷ ጋራ ተስማተን ነበር» አባትዬው ግን በቂ ሀብት ጠያቂ እየሆኑ አስቸገሩ» አለኝ።

«እንዴት?» አልኩት

«በአጥንት በኩል ያለውን ፈተና አልፌዋለሁ፤ አባትዬው ብቻ አንጃ ግራንጃ ያበዛሉ» አለኝ።

«ታዲያ ሌላ ትለውጥም?» ብለው አሁንም ራሱን አካከከና «አለውጥም፤ እከካም አግብቼ ሳክ ከምኖር እሷኑ ማግባት እመርጣለሁ» አለኝ።

«እንዴት?» ብለው፤

«የትልቅ ሰው ልጅ ናት፤ አባትዋ መከታ የሚሆኑ የስሚንቶ ግምብ ናቸው» አለኝ።

«ሀብታቸውን ነው የምትለው?» አልኩት

«አዎ ሀብታቸውም ቢሆን ቢያዳልጥ የማይጥል ነው» አለኝ።

«አንተ ሀብት የለህም እንዴ?»

«አለኝ»

«ለምሳሌ ምን ያህል እንዲኖርህ ይፈልጉብሃል? አንተስ ምን ያህል አለህ?» ብዬ ጠየኩት።

«የዛሬው ጋብቻ ያስቸገረው ወላጆች በነገሩ መሐል እየገቡ ነው?» አለኝ።

«ወላጆች ወልደው መጣልን ስለማይፈልጉ» አልኩት እኔ ደሞ «ወላጆች ወልደው መጣልን ስለማይፈልጉ ነገሩን ቢያጣሩ አያስከፋም፤ እኔም እንደዚሁ እንዳንተው አጭቼ ነበር፤ ምን ይሆናል ታዲያ ደሀ ነው ብለው ከለከሉኝ፤ አንተ ግን ሀብት ስላለህ ልታገባ ትችላለህ።»

«ማግባትስ እችላለሁ» አለኝ እሱ ደሞ «ግን» አለና አቅማማብኝ

«ቆይ እንግዲህ መቼም ጨዋታ ነውና ምን ያህል ሀብት ቆጥረህላት ነው ማግባት የምትችለው?» አልኩት።

«ልጅቷ እርግጥ ወዳኛለች፤ ደግሞም ማግባት አለብኝ፤ ይህም ብቻ ሳይሆን በእርግጥ እሷን ማጋብት አለብኝ» አለኝ።

«አንተ በቂ ሀብት ካለህ ምን ያለማምጥሃል?» ብለው፤

«አዎ»አለና «ቢሆንም» አለኝ።

«ቆይ ለምሳሌ» አልኩት «ለምሳሌ አባትዬው ያለህን ሀብት ቁጠር ቢሉህ ልትቆጥር የምትችለው ምን ያህል አለ?»

«እችላለሁ፤ ብቻ በስሜ እስካዛውረውና እስከደላደል ቃል ገብተው ቀለበት አሥረን ለጋብቻ ጊዜ ይስጡኝ እንጂ በሚገባ እቆጥርላቸዋለሁ፤ ማጨቴም በዚያው ተመከቼ ነው» አለ።

«ለምሳሌ በኔ የደረሰ ፈተና እንዳይደርስብህ ስትደላደል ምን መቁጠር ትችላለህ?» አልኩት «አንተ ምን ዓይነት ፈተና ነው የደረሰብህ» አለኝ።

«ይሔማ መንገድ ልመራህ ነው» አልኩትና ወዲያው ደግሞ «ያንተን ከነገርከኝ በኋላ የኔን እነግርሃለሁ፤ መቼም ጨዋታ ነው፤ ፊልምም አልሔድንምና ቀኑ እንዲመሽልን በሰፊው እንጫወት» አልኩት።

«ደኅና ነው በል ያናተን አውራልኝ» አለኝ።

«ኖ በፊት እንደጀመርከ ያንተ ጨርስ» አልኩት

«የኔን ነግሬሃለሁ፤ ሀብቴን ቆጥሬ ማግባት ነው» አለኝ።

«ልክ በኔ የደረሰ ፈተና እንደሚያጋጥምህ ይሰማኛል፤ ካሁኑ ማጥናት ያስፈጋል፤ ቆይ ምን ትቆጥርለህ?» አልኩት።

«በጠቅላላው ቢበዛ በመቶ ሺህ ብር የሚገመት ቢያንስ ሃምሳ ሺህ ብር የሚገመት ሀብት አለኝ» ሲለኝ ደነገጥሁ፤ «በጣም ጥሩ» ብዬ ሳልጨርሰው አቋረጠኝና «እመነኝ ደግሞ እንደ አራዳዎቹ ልጆች የምዋሽ አይደለሁም፤ ልጅቱም ታውቃለች፤ በሰፊው ስላስወራሁት አባትዬውም ቢሆኑ ሰምተውታል። ብቻ ጥቂት ጊዜ እንዲጠብቁኝ ያስፈልጋል» አለኝ።

«በውርስ የምታገኘው ነው?» አልኩት

«እናት አባቴ በልጅነቴ ነው የሞቱት» አለኝ።

«ወርሰሃል ማለት ነዋ» አልኩት።

«አልወረስኩም» አለኝ።

«ታዲያ ባንተ ዕድሜ እንዴት የመቶ ሺህ ብር ሀብት ለማጠራቀም ቻልክ» አልኩት።

«ቀላል ነው» አለኝ፤

«እንዴት?» አልኩት፤ ሻይ የጠጣንበትን ፍንጃል ከፊታችን እያነሳሳ «በመጀመሪያ ቀለበቱን ልሠር እንጂ የሀብት ነገር ሞልቷል» አለኝ።

«አሁን ለቀለበቱ ጊዜ አለኝ የምለውን ሀብት ልትቆጥር ትችላለህ?» ብለው ከተቀመጥኩበት ከፊቴ ትንሺ ጠረጴዛ አጠገብ ቆሞ ቁልቁል እያየኝ «አይገባቸውም እንጂ እችላለሁ» አለኝ።

«እንዴት አይገባቸውም? ካለህ አለህ ማለት ነው» አልኩት፤

«አንጃ ግራንጃ ያበዛሉ» አለኝ፤

«ምንድነው አንጃ ግራንጃው?» ብለው

«የተጨበጠ ማስረጃ ይፈልጋሉዋ» አለኝ።

«አንተ የተጨበጠ ማስረጃ የለህም እንዴ?» ብለው፤

«አለኝ» አለና ፈገግ ብሎ ከኪሱ ቦርሳውን አውጥቶ «ይሄ ደሞ ሁሉ የማረገው ነው» እያለኝ ከቦርሳው ውስጥ የብሔራዊ ሎተሪ ቲኬት ሙሉ ሴሪ አሳየኝ።

# ለ፳፬ ሰዓት

በልጅነቱም ሥራ ይወድ ነበር፤ የአስተማሪዎቹን ቤት ጠርጎ የትምህርት ቤቱን ግቢ ሁሉ ሳይታዘዝ ያጸዳ ነበር፤ በእረፍት ቀኑ በየጫካው እየዞረ እንጨት መቁረጥ፤ ድንጋይ መፍለጥ ይወድ ነበር፤ በጠቅላላው መቀመጥ የማይወድ ቱን ቱን ባይ ነበር።

እናቱ እማሆይ አመተየስ እንደዛሬ ሳይመለኩሱ «ጧሪዬ ልጄ አሸናፊ ነው፤ ሌሎቹስ ፈሎም የላቸው» ይሉ ነበር፤ እውነታቸውን ነው፤ የአሸናፊ እኅቶች እነ መዓዛ እነ በለጠች ከልጅነታቸው ጀምረው የሚወዱት ሻሽ ማሠር፤ ጠጉር ማበጠር፤ መሽቀርቀር ነበር፤ ያው ያደጉበት ሆኖ ነው በለጠች አሁን ከበረሃው የምትኖረው የአሸናፊ ታላቅ ወንድም ኃይሉም ቢሆን ማላጋ ማጋጣ ነበር፤ አሁን ያው ነው።

ኮስታራው አሸናፊ የሆነ እንደሆነ ሳይቆነጠጥ እንደ ተቆነጠጠ ሆኖ ያደገ ነው፤ ከልጅነቱም ጀምሮ ሐሳቡ ራሱን የሚችልበትን በሞያው ከጓደኞቹ የሚበልጥበትን መንገድ ማሰላሰል ነው።

አድጎ ሥራ ከዚያም በኋላ በሥራው በሞያው ተወደደ አሸናፊ ሥራው ብቻ ሳይሆን አመሉ ጠባዩ ሰው የማይነካ ቢያነጥፉት የማይቆረቁር በመሆኑ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች በሙሉ ይወዱታል፤ ከበደ እንኳ

«ክንፍ ያላበቀለ መልአክ ነው፤ እያለ የሚያወራለት በዚሁ በጠባዩ ነው።

ላለቆቹ መታዘዝንና ካለቆቹ ጋር መግባባትን ይወዳል፤ አሽናፊ ከውዝፍ ሥራዎቹ ጋር መግባባትን ይወዳል፤ አሽናፊ ከውዝፍ ሥራዎቹ ጋር የተጋጠመ እንደሆነ አፈር ድቤ ያስግጣቸዋል፤ በዚሁ ሥራ በመወደዱና በመሥራቱ ነው አንዴ ባንድ ጊዜ የሙቶ ብር ጭማሪ ያገኘው።

አለቃው አቶ ዱባለ አሽናፊ ካለ እያሉ የመኩበታል፤ እውነት አላቸው እንዴ ከበላይ አንድ አስቸኳይ ሥራ ታዘው የሚሠራልኝ አሽናፊ ነው ብለው እንደተመኩበት ባንዴ አከናውኖ አስደስቷቸዋል።

ባዘዙት ቦታ የሚውል ሠራተኛ ነው፤ መፎካከር መስነፍ አይወድም፤ እነ እከሌ እያሉ ምነው እኔ ብቻ የሥራ ሸክም በእንጉብዴ የምሸከመው አይልም፤ በላይ በላዩ የሚጨመርለትን ሥራ በደስታ ይቀበላል፤ የራሱ ጨርሶ የሌሎቹን ፈንታ የሚያካሒድ ሠራተኛ ነው።

በዚሁ በሥራ ወዳድነቱና በሥራው ከለቃው ካቶ ዱባለ ጋር ተስማምቶና ተዋዶ ይኖራል፤ ለጥቂት ዓመታት ያህል በዚህ ዓይነት ሲሠሩ ኖሩ፤ በኋላ የቅያሬ ተራ ደረሰና አቶ ዱባለ ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት ተዛወሩ። ባቶ ዱባለም ቦታ አቶ መኮንን ሆኑ።

እነ አበበ የዚህን ጊዜ የመግቢያ ቀዳዳ መኮንን ገና የተሾሙ ዕለት እነ አበበ ባለሟሎቻቸው ሆኑ፤ ወዲያውም በመሥሪያ ቤቱ ስላሉት ሠራተኞች ስለ እያንዳንዳቸው ላቶ መኮንን ማስጠናት ጀመሩ።

ባቶ ዱባለ ጊዜ እነ አበበ በስንፍናቸውና በለጋሚነታቸው ታውቀው ሁልጊዜ የሚቀጡ ነበሩ፤ አቶ ዱባለም ይህንንኑ የሚሠሩ መሆናቸውን አወቀውባቸው ለማንኛውም ሥራ አይጠሩዋቸውም ነበር፤ ፈጽመውም አያዟቸውም ነበር፤ በጠቅላላው ያለ ዕድሜያቸው የሚጦሩ የመሥሪያ ቤቱ ጡረተኞች ነበሩ።

የሹማምንት መለዋወጥ ለአባይ ያመቻልና እነ አበበ ካቶ መኮንን ጋር ልጥፍ ብለው የሚወዱትን እያስወደዱ የሚጠሉትን ያስጠሉ ጀመር፤ በዚህ መሐል በደሞዝም በአሠራርም ይበልጣቸው የነበረውን አሽናፊን ሲመቀኙት ኖረው ነበርና ባቶ መኮንን ዘንድ እንዲጠላ አደረጉት።

አቶ መኮንንም የነ አበበን ሰምተው አሽናፊን ስለ ጠሉት ይወቅሱትና ያኳስሱት ጀመር፤ አሽናፊ የሚሠራው ሥራ ሁሉ አቶ መኮንንን ያስጠላቸው ጀመር፤ ለፊርማ የሚያቀርቡላቸውን ሁሉ ይቆይ እያሉ ያቆዩና ከነ አበበ ጋር ተማክረው ፈጽሞ የማይረባ ሥራ መሆኑን ይረዱና የሱን ቀደው እነሱ እንዲሠሩ ያደርጓቸው ጀመር።

እየቆየ አሸናፊ ምንም እንደማያውቅና እንደማይሠራ ያህል ስለታሰበ ተራ ደረሰበትና በተራው የመሥሪያ ቤቱ ተጧሪ ሆነ፤ ደደብ ነህ ደደብ ነህ ስላሉትም አሸናፊ ደደበ፤ እነ አበበም ቀስ በቀስ ካልቃው ጋር ይብስ ያቃቅሩት ጀመር፤ አሸናፊም ሲጠሩት የማይሰማ ሲነገሩት የማይገባው ሆነ።

አንድ ቀን አቶ መኮንን ከነ አበባ ጋር ስለ አሸናፊ ሲያወሩ «ሲጠሩት የማይሰማ ሲነግሩት የማይገባው ምን ደደብ ነው» ቢሉ አበበ ፈጠን አለና «ጌታዬ ተፈጥሮው ነው» አላቸው።

«ታዲያ እንዴት ይህ ሁሉ ደሞዝ ተቆለለበት?» አሉ አቶ መኮንን፤

«በዘመድ ነው» አላቸው አበበ፤

«ድሮም ደንቆሮ ነበር ወይስ አሁን ብቻ ነው?» አሉ፤

«ድሮም ደንቆሮ፤ ነው» አላቸው አበበ፤

«እንግዲያማ ደንቆሮ ከሆነ» አሉ አቶ እምኮንን «ከፔርሶኔል ክፍል ይዛወር» ቢሉ ዓለሙ ቀበል አደረገና «ጌታዬ ሥራን ያበላሸዋል፤ እሱ እንደሁ አይሠራ» አላቸው።

«ባይሠራም» አሉ አቶ መኮንን «ከሥራ ጠያቂዎች ጋር ይስማማልና ከዚያ ሆኖ ይደናቆር» አሉና የመዛወሪያ ማዘዣ ተጻፈ፤ አሸናፊም ማዘዣው እንደ ደረሰው በቀጥታ ወደ ፔርሶኔል ክፍል ተዛወረ።

አሸናፊ የጁን አገኘ ይባል ጀመር፤ የሚሠራው ነገር ስላጣ እየተበሳጨም እየተናደደም የሌለበትን ዓመል ሲጀራ ማጨስን ጀመረ፤ ለስድስትው እራት ያህል እንዲህ ሆኖ ከኖረ በኋላ አቶ እምኮንን እንዲለወጡ ማዘዣ ደረሳቸው ባቶ መኮንንም ፈንታ አቶ ልኬለህ መጡ፤ አቶ መኮንንና አቶ ልኬለህ ሲረካከቡ አቶ መኮንን ሠራተኞቹን ሁሉ ካቡና አሸናፊን እንደ ተረሳ ዕቃ ረሱት።

አሸናፊ በተፈጥሮው መለማመጥ አይወድም፤ ካለቆቹ ጋር ሲገናኝ የሚፈለግበትን ሳይሆን ተገቢውን ሰላምታ ይሰጣል። እጅ እነሳሱም ካንገቱ ቀልበስ ማለት ብቻ ስለሆነ አብዛኛውን ካለቆቹ ጋር የሚያጣላው ይሔው ነው።

አቶ መኮንን ሥራችወን ላቶ ልኬለህ ሲያስረክቡ አሸናፊን ከነዶሴው አስረከበውለታል፤ ጥሩ አልነበረም፤ ዶሴው የበከተ ነው፤ ብዙ ወንጀል ተጽፎበታል፤

የማይሠራ መሆኑን ይናገርበታል፤ በተለይም ወደ ፔርሶኔል ክፍል ሲዛወር የተጻፈበት ቀላል ደብዳቤ አልነበረም።

አቶ መኮንን በቃልም ደኅና አድርገው አስጠንተውለት ስለ ነበሩ አቶ ልኬለህ አሸናፊን በዘመድ የገባ ሽክም ይሉት ጀመር፤ ለነ አበበ እንደ ገና ካቶ ልኬለህ ጋር ስለ ተወዳጁ አሸናፊ አሁንም የመውደቂያው ነገር እንጂ የመነሻው የማይታሰብለት ሆነ።

እንደ ገና በየዕለቱ ስሙን የሚያጠፉ ደብዳቤዎች ይጻፉለት ጀመር፤ ያላሰበው ነገር ሁሉ ወንጀል እየሆነበት ተገኘ። ለሚረባውም ለማይረባውም ነገር በቃል ጥያቄ ለሚፈጸመው ሁሉ ደብዳቤ ይጻፍለት ጀመርየግል ማኅደሩ እንደ ገና ብሶ በከተ፤ የሚፈልገውም ይሄው ነበር፤ ሆነ።

እየተበሳጨና እየተናደደ እንደ ገና በሲጃራው ዓመል ላይ የመጠጥ ዓመል ተጨመረበት፤ ፌዘኛና አልምጥ ሆነ፤ ሚስቱ አስካለም ዘወትር በትመከረውና መበሳጨቱን እንዲተው ብታባብለውም የማይበገር ሆነ።

በዚሁ በመስከሩ በመሥሪያ ቤቱ ተወነጀለና ተሰሰሰ፤ የአሸናፊንም ክስ የሚመለከተው ኮሚቴ ተቋቋመ። «በመሥሪያ ቤቱ ሥራ የለውም፤ ከዚህም ሌላ ሰካራም ሆኖ ከተገኘ ከሥራው ይወጣል» ሲሉ ግማሾቹ ፈረዱበት።

አሸናፊ ደግሞ ከኮሚቴው ቀርቦ «ሰክሬ ስሥራ አልተገኘሁም፤ በቢሮም አልረበሽሁም፤ ምንጊዜም ቢሆን ሰክሬ ከቢሮ አልገባሁም ሥራ የተባልኩትን እሠራለሁና ጥፋተኛ አይደለሁም» ሲል እከራከረ። «ምንም እንኳን ሰክረህ በቢሮ ባትረብሽም መስከርህ ራሱ ኃጢአት ስለሆነ መቀጣት ይገባሃል» ብለው ኮሚቴው አቶ ወርቁ ፈረዱ።

አሸናፊ ሲመልስ «ስካር ኃጢአት ነው ለሚባለው ባዩ በስማይ ያለው ይቅጣኝ፤ በታችኛው በናንተ ቤት ግን አያስፈርድብኝም፤ መሥሪያ ቤቱ የሚሰጠኝን ደሞዝ ለፈለሁት ላውለው መብት አለኝ፤ ለተወሰነ ነገር አውጣ የሚለኝ ሕግ የለምና አልቀጣም» አለ።

የኮሚቴው ዳኞች ማጣፊያው ስላጠራቸውን አሸናፊን ላይቀጡት ተስማምተው ነበር፤ አቶ ልኬለህ እንደሚቀየሙዋቸው ስላወቁ አሸናፊ ከሥራ መውጣጡ ቀርቶ በሃምሳ ብር ቅጣት እንዲታለፍ ወሰኑ፤ አሸናፊም የማንገራገሪያው መንገድ ስለታጠረበት ሳይወድ በግድ አሜን ብሎ ቅጣቱን ተቀበለ።

አሸናፊ ተንኮለኛ ሆነ፤ ካለቃውም ጋር ብሶ ተቃቃረ፤ ሲያገኛቸው እጅ መንሳቱንም ተወ፤ አለቃውን እጅ እንዲነሳ የሚያግባቡትም ሰዎች ለምን እጅ አትነሳቸውም? ሲሉት «ጢት ጢት ቅቤ እየጠጣሁ ስለምወጣ ጎንበስ ስል ፍልቅ እንዳይልብኝ እየሰጋሁ ነው» ይላቸዋል።

አቶ ገብሬም አሸናፊን ካቶ ልኬለህ ጋር ለማግባባት ሞክረው ነበር፤ አቶ ልኬለህ «ጠግቧል ፍጹም የሥራ ሰው አይደለም፤ እሱው ራሱ በጥጋብ ተጣላኝ እንጂ

እኔ አልበደልኩትም» ብለው ላቶ ገብሬ ይነግሩዋቸዋል፤ አሽናፊን ደግሞ ሲጠይቁት «ተበደልኩ እንጂ አልበደልኩም» ስለሚል አቶ ገብሬ ነገሩ ትተውታል።

አቶ ልኬለህና አሽናፊ በተንኮል እምገድ ይፈላለጉ ጀመር፤ አየለ የአያቱን አርባ ደግሶ የመሥሪያ በቱን ሠራተኞች በሙሉ ጠርቶ ነበር፤ በእርግጥ ጥሩ ድግስ ደግሶ ነበር፤ አየለ ከመኳንንት ቤት ያደገ በመሆኑና አያቱንም በጣም ስለሚወዳቸው ድል ያለ ድግስ ደግሷል።

የተጠራው ካህናት ብዙ ነው፤ ጠፍ ያለለት ጮማ ይቆረጣል፤ ጠጅ በብርጭቆ እንደ ጠላ ይቀዳል፤ ሞልቷል፤ ይበላል ይጠጣል ድግሱ ተረፍረፍ ያለ ነው፤ አሳላፊዎቹ አስተናባሪዎቹ ተጋባዦቹ እንዲደሰት የሚያስቡ ናቸው በዚሁ ነው ሞቅ ያለው አሳላፊ የበዛው፤

ምሳ ተበልቶ ገበታው ከፍ ካለ በኋላ አቶ ልኬለህ አንድ ሁለቷን ስበው ኖሮ አፋቸው ነጠቅ ነጠቅ ይል ጀመር፤ ሌላ ሰው ባያወራና እሳቸው ብቻ ቢያወሩ ወደዱ፤ ስለሠሩት ሥራ ሊሠሩ ስላቀዱት ፕላን፤ እንዴት ተመስጋኝ ሰው እንደሆኑ መሥሪያ ቤታቸው ቀርቶ ዓለም ሁሉ ባጭሩ አዳሜ በሙሉ በሥራችወ የሚደነቅ ስለመሆኑ ነበር አቶ ልኬለህ የሚያወሩት።

ቢሆንም ወሬአቸው እንደ ድሮው አልነበረም ነጠቅ ያደርጋቸዋል፤ ምላሳቸው ተያይዞ ኮልተፍተፍ ይላል፤ ሰዓት ደረሰና ወደ ሥራቸው ለመሔድ ሲነሱ ጠረጴዛውን ነኩትና ከብርጭቆዎቹ መሐል አንዱ ወድቆ ተሰበረ፤ ሲወጡም ጥንጁት በመሰለው ዓይናቸው መንገዳቸውን እያዩ ወልገድገድ እያሉ ሔዱ፤

«እማኞቼ ናችሁ» አለ አሽናፊ «በኋላ በነፍሳችሁ ነው የምመጣው መስከራቸውን እወቁልኝ። ልብ ብላችሁ እዩልኝ» አለና ከበደን ተፈሪን፤ ገዛኸኝንና ራሱንም አበበን አሳመነ፤ ወዲያውኑ በዘጠኝ ሰዓት ከሥራ ሲገባ የክስ ደብዳቤውን ጽፎ ያኔ ለሱ ስካር ጊዜ የተመረጡት ኮሚቴ አባሎች አቀረበ። «እኔ ሳይመሰከርብኝ ትሰክራለህ ተብዬ ሃምሳ ብር ከተቀጣሁ አቶ ልኬለህ ግን በኛ በሠራተኞቻቸው መሐል ሰክረው ተገኝተዋል፤ ስካሩ ሳይበርድላቸውም ከቢሮ ገብተው የመንግሥቱን ሥራ ሲያበላሹ ውለዋል፤ ለዚህ ሁሉ ምሥክሮች አሉኝና ይቀጡልኛል» ሲል ማመልከቻውን ጽፎ በግልባጭ ለበላይ መሥሪያ ቤት አሳወቀ።

ቢልም ቢለፋም አለቃውን ሊያስቀጣ አልቻለም፤ ከበላይም ዘንድ ለዚሁ ብሎ ቢመላለስም አቃተው፤ እንዲያው የቀረበው ክስ የራሱን ሞያ የሚያጠፋበት በመሆኑ የበላዮች ታዘቡት እንጂ ፋይዳ አልሠሩለትም፤ ቀርቦም ቢጠይቅ ታዘብንህ» አሉት። «ለምን/» ቢል

«ነግ በኔ» አሉት፤ እስተነአካቴው የበላዩን የሚደፍር በመሆኑ ለሁለተኛ ጊዜ እንዳይደግም ማስጠንቀቂያ ተጻፈለት፤

በኋላም ሽማግሌዎች በነገሩ መሐል ገቡና ፈፅመው በተንኮ ላይፈላልጉ ቃል አስገብተው አስታረቋቸው፤ አሸናፊም እስከ ጭራሹ ትቷት የነበረችውን ያቺኑ የድሮ እጅ አነሳሱን ጀመረ፤ አቶ ልኬለህም አሸናፊን ለመግዛት ያህል አልፎ አልፎ እጁን በሰላምታ ይጨብጡት ጀመር። ሁለቱም ካንገት በላይ ለመተላለል ያህል ተግባብተው የሚሠሩ አለቃና ጭፍራ መሰሉ።

አሸናፊ «አባትህ በጠና ታመዋልና በነፍስ ድረስ» የሚል ቴሌግራም ከሐረርጌ ደረሰው፤ እውነት ነው፤ አባቱ ታመውበት ነበር፤ አሸናፊ ቴሌግራሙ እንደ ደረሰው እኒያ ድሃ አባቱ በደደር ውርጭ ከዚያች ደሳሳ ጎጆአቸው ድፍት ብለው ታዩት፤ የጠፍር አልጋቸው ቁርቋሬ፤ የአገልጋያቸው የእንኮዬ ደማሜ ንትርክ፤ የገበሬያቸው የአልዩ ለጋሚነት የፋጤና የአሻ ደባድባሳነት ሁሉ ከፊቱ ተደቅኖ ታየው። ባባ፤ የአባቱ ናፍቆት ሆዱን አሸበረው።

ራሱን የደረሰውን ቴሌግራም ይዞ ማመልከቻውን ጻፈና የስምንት ቀን ፈቃድ ለመጠየቅ ካቶ ልኬለህ ቢሮ ገባና ከወትሮ አብልጦ እጅ ነሣና ማመልከቻውን ሰጣቸው።

«ሥራ በዝቶብናልና አይቻልም» አሉት።

«ጌታዬ የአባት እንገር ነውና እባክዎ ይፍቀዱልኝ» አላቸው አሸናፊ፤

«እኔ አልፈቅድልህም የምችለው ለአንድ ቀን ነው፤ ከዚያ በላይ አልችልም» አሉ አቶ ልኬለህ።

ካቶ ልኬለህ ጠረጴዛ ፊት የቆመው አሸናፊ «በሊቶሪን ድሬዳዋ ደርሼ ለመመለስ እንኳ ጊዜው ብቻ ሁለት ቀን ይፈጅብኛል፤ ካባቴ ጋር ያንድ ቀን መተያየት ይበቃኛልና እባክዎ የሦስት ቀን ፈቃድ ይስጡኝ» አላቸው።

ጠረጴዛውን ተደግፈው የተቀመጡት አቶ ልኬለህ ፈገግ አሉና «አይሆንም እንጂ ከሆነማ ምንቸገረኝ ነበር፤ ከፈልግህ ያወም ላንተ ሥል ነው ያንድ ቀን ፈቃድ እሰጥሃለሁ» አሉት። አሸናፊ ለጥቂት ጊዜ ተክዞ ቆየና መልሰው የሰጡትን ማመልከቻውን እንደገና አቅርቦ «እባክዎ ጌታዬ የዛና ይለመኑኝ» ቢላቸው አቶ ልኬለህ ማመልከቻውን ከአሸናፊ እጅ ነጠቁና «ስነግርህ አትሰማም?» አሉና ለመገላልገህ ያህል በንዴት «ለ፳፬ ሰዓት ብቻ ፈቃድ ተሰጥቶታል፤ ከዚያ ቢያልፍ ደሞዙ ተመላሽ ይሁን» ብለው ጻፉና ፈረሙ።

እሮብ ዕለት ፈቃዱን ተቀብሎ በማግሥቱ ሐሙስ ወደ ድሬደዋ ሊወርድ ተነሳ፤ እላጋር ድረስ ጓደኞቹ ሸኙት ከሸኚዎቹ መሐል ኃይሉ «አትሒድ ይቅርብህ ለነገ ጧት ሥራ ልትደርስ አትችልምና እባክህ አትሒድ» አለው፤ አሸናፊ ግን የለም እሔዳለሁ አለ።

ዘለቀም «ሰውዬው ሰበብ ነው የሚገልጉብህ ደሞዝህን ይቆነድዱሃል፤ ወይም ደግሞ ከሥራ አይገባምና ከሥራው ይወገድ ይሉሃል» ቢለው አሸናፊ ነደድ አለውና «እስከ መቼ ነው አለቆቻችንን እንደ ፈጣሪያችን የምናያቸው? መቼ ነው እነሱን ይጎዱናል እያልን ከማሰብ የምንድነው? ኧረ እንዲያው መቼ ነው እንዴ ምን ማለታችን ነው? እኔም እኮ መብት አለኝ አላቸው።

«ተው እንደሱ አትበል› አለ ዘለቀ «አፍህን ሰብስብ እርግጥ መብት አለህ፤ ግን ካንተ ይልቅ አለቆችህ ይሰማሉ፤ ስለዚህ እነሱን ከመለማመጥ ሌላ የሚያዋጣ የለንም እባክህ ቅር» አለው አሸናፊ ግን «እሔዳለሁ» አለ።

ባላገሩ ሜዳ ላይ እየተንጎራደዱ «አባትህም በጎ ሳይሆኑ አይቀሩም ቶሎ እንድትሔድላቸው ይሆናል በነፍስ ድረስ ያሉህ» ሲለው አሸናፊ ነጠቅ አደረገና «እግዜር ይመስገን ትናንት ማታ ከራሚስ የመጣ ሰው እግኝቼ በጎ መሆናቸውን ነግሮኛል» አላቸው ለጓደኞቹ።

«እንግዲያውስ» አለ ኃይሉ «አትሒድ ከዚህ ሞዛዛ ሰው ጋርም አጉል ጠብ አትጫር ደህና የታረቃችሁትን እንደ ገና አታበላሽ ለሱም መንገድ አትስጠው፤ በሥልጣኑ እንዲሠራብህም መንገድ አትከፈትለት» ቢለው «የለም እሔዳለሁ» ሲል አሁንም መለሰ

«ለጠብ ፍለጋ?» አለ ዘለቀ

«ለሰላም ነው» ሲል መለስ አሸናፊ

«እንዴት ሰላም ይሆናል? የተቀበልከው ያንድ ቀን ፈቃድ ነው፤ የምትሔደው ይደር ነው፤ ሊቶሪን ነችና ዛሬ ማታ በኩፌራ ይደር ትደርስ ይሆናል፤ ያውም ቀርሳ ላይ ያለው መንገድ ጭቃ ሆኖ ያልያዛችሁ እንደሆነ ነው፤ ፈቃድህ ያንድ ቀን ነው፤ ነገር ከሥራህ መግባት አለብህ፤ ታዲያ እንዴት ለሥራህ መድረስ ትችላለህ?» አለው ታዲያ እንዴት ለሥራህ መድረስ ትችላለህ?» አለው ዘለቀ።

ኃይሉ ደግሞ ቀጠል አደረገና «እውነትህን ነው የሰውየው ፈራረም ለተንኮል ነው፤ እንግዲያውማ ጨለንቆ ነው የተወለድሁት ይል የለ፤ ያውቃል፤ ባንድ ቀን ደርሶ መልስ የማይገባበት ሀገር መሆኑን ያውቃል ለተንኮል ነው ላንድ ቀን ብሎ የፈረመልህ ብትቀር ሊቆነድድህ ወይም ሊያስወጣህ ነው፤ ብሷልም ከማመልከቻህ ላይም ጽፏል፤

ቢቀር ደሞዙ ይመልስ ብሏላ ከሔድህ በውሳኔው መሳማምትህ ነው፤ ልቀጣ ብለህ ነው? እባክህ ቅር» አለው።

«የፈለገው ይሁን እንጂ አልቀርም» አለ አሸናፊ ዘለቀ ደግሞ «ቅር ነው የምንልህ አሁን ደህና መሆናቸውን ሰምተሃል ቀስ ብለህ እነጋሽ ለማን አማላጅ ልከህ የስምንት ቀን ፈቃድ ተቀብለህ ብትሔድ ይሻልሃል» አለው።

«ለኔ ብላችሁ እንደምትመከሩኝ አውቃለሁ» አለ አሸናፊ ሲመለስ «ግን እሔዳለሁ ብዬ ፈቃድ ተቀብያለሁና መሔድ አለብኝ ውሸታም አልሆንም» አለ።

«ከመጣላት ብትቀር ይሻልሃል» ዘለቀ ሲለው ቲኬት ማስቆረጫው በር ስለተከፈተ አሸናፊ ፈጥኖ ሔደ፤ ኃይሉና ዘለቀም ቆርጦ ነበርና ሳያመነታና ሳያወላውል ቲኬቱን አስቆርጦ ተሳፈረ።

ኃይሉና ዘለቀ ከመሬት ሆነው በሊቶሪናዋ መስኮት ብቅ ያለላቸውን ጓደኛቸውን አሸናፊን እንዲቀር ያባብሉት ጀመር፤ በመጨረሻም ተስፋ ስለ ቆረጡ፤ «የማዝነው ቃሌን ባለመስማትህ ነው፤ ዛሬ ድሬደዋ ገብተህ ነገ ብትመለስ እንኳ የፈቃድህ ቀን ባንድ ቀን እልፊት ያልፋል፤ እምቢ ብለኸኛልና የሚደርስብህን መከራ ያሁኑ ያስታውስሃል» እያለ ኃይሉ ሲነግረው ሲቶሪናይቱ ጉዞዋን ጀመረች። አሸናፊም በፈገግታ ራሱን እያወዛወዘ ምንም አልደረገ እያለ ተሰናብቷቸው ተጓዘ።

አሸናፊ ይግረማቸው ብሎ ሐሙስን አርብን ቅዳሜን ካባቱ ዘንድ ከረመና እሑድ በማታ ባቡር ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ሰኞ ልክ ስድስት ሰዓት ላይ ወደ መሥሪያ ቤቱ ሔዶ ካለቃው ቢሮ ገባ።

ወዲያውኑ እጅ ነሳና «ጌታዬ የፈቃደኢን ጊዜ ጨርሼ በደህና ተመለስኩ» አላቸው አቶ ልኬለህ አገጫቸውን በእጃቸው ደግፈው እንደተቀመጡ «ጥሩ ነው፤ የፈቃድህማ ጊዜ ሐሙስ ዕለት አልቋል» አሉ፤

«የለም ገና አሁን ማለቁ ነው» አላቸው፤

«የሰጠሁህ ላንድ ቀን ነው» አሉት፤

«አይደለም» አላቸው፤ አቶ ልኬለህ አሸናፊን ገላመጡትና «ነው እንጂ ደሞ ውሸታም ልታደርገኝ ነው?» ቢሉት አሸናፊ በለሆሳስ አተርኩሮ እያያቸው «አይደለም» አለ።

«ነው» አሉት።

«አይደለም» አለ

«ምን መሆኑ ነው?» አሉ፤

»ምንም አልሆንኩ» አለ፤

«ስትከደኝ» አሉ፤

«አልካድኩም» አለ፤

«የሰጠሁህ ያንድ ቀን ፈቃድ ቀን አይደለም?» ብለው ጠየቁት፤

«አይደለም» አላቸው፤

«ጤናም አይደለህ? ዓይን ባይን ትክዳለህ?» አሉት

«አልካድኩም» አለ፤

«ኋላ ምን ማለትህ ነው?» ብለው አቶ ልኬለህ ጠየቁት።

«አለመካዴ ነው» አላቸው።

«የሰጠሁህ ያንድ ቀን ፈቃድ ነው አይደለም?» ቢሉት።

«አይደለም» አላቸው፤ አቶ ልኬለህ በስጨት አሉና በንዴት ደወል ደወሉ፤ ተላላኪው ሲገባ «የአሸናፊን ዶሴ አምጣ» አሉትና ሔደ፤

ዶሴው እስኪመጣ ድረስ ከአሸናፊ ጋር ይወዛገቡ ጀመር፤ «ኸረ ለመሆኑ ምን ያልኸው አባይ ነህ» ምስክር ያለውን ነገር ትክደኛለህ» ቢሉት አሸናፊ እጆቹን አጣምሮ እንደ ቆመ «አልካድኩም» አለ።

«አይ እንግዲያው እኔ ከፈረምኩ በኋላ ከመዝገብ ቤቶቹ ጋር ተስማምተህ የአምስት ቀን ፈቃድ ብለህ ደልዘህ እንደሆን አላውቅም፤» ቢሉ «አልደለዝኩም» አለ።

«ካልደለዝከው ታዲያ የፈረምኩልህ እኔ አይደለሁ?»

«ነዎት»

«ታዲያ እንዴት ዓይንህን ጨፍነህ ትዋሻለህ?»

«አልዋሸሁም» አለ።

ወዲያው ተላላኪው ዶሴውን ስላመጣ አቶ ልኬለህ እንደተናደዱ በኃይል ገለጥ አደረጉና «ታዲያ ይሔ አይደለም?» አሉና አንዴ ወረቀቱን በቃርያ ትፊ መትተው በአሸናፊ ላይ አፈጠጡበት።

አሸናፊ ረጋ እንዳለ «ምን ይላል?» አላቸው፤

«ለ፳፬ ሰዓት ብቻ ነዋ» አሉ፤

«ታዲያ ምን አጠፋሁ» አለ፤

«ደሞ አሁንም እኮ አያምንም» ቢሉ፤

«አምኛለሁ» አለ፤

«ከተሰጠህ ፈቃድ በላይ መቆየትህን አመንህ?» ቢሉት

«አላመንኩም» አላቸው

«ምን ይመናቸካል» አሉና «እንዴት ነው ያላመንከው?» አሉ።

«ያስቡታ ጌታዩ» አላቸው፤

«እንዴት አስበዋለሁ ሃያ አራት ሰዓት አንድ ቀን ነው» አሉት፤


«የሰጡኝ ፈቃድ ለ፳፬ ሰዓት ከሆነ ልክ ቅድም እዚህ ስደርስ የፈቃድ ሰዓቴ አለቀ» አላቸው።

«ባንተ ቤት ፳፬ ሰዓት ማለት አምስት ቀን ማለት ነው?» አሉ፤

«አይደለም» አላቸው

«ታዲያስ?» ቢሉት፤

«ሊፈቅዱልኝ የሚችሉት በሥልጣንዎ ሥር ለምሆንበት ሰዓት ብቻ ነው፤ የፈቀዱልኝ የ፳፬ ሰዓት ፈቃድ ልክ ዛሬ ሰኞ በስድስት ሰዓት ላይ ያልቃል»



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታችው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም 19 መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸ። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)
2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)
5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)
6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)

8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)
9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)
10. እውቀት (**ፍልስፍና**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY